አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ
## የተማሪ መጽሐፍ



## ፬ኛ ክፍል

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፬(4)ኛ ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ


አዘጋጆች

ምስጋናው ነገሰ ዘለቀ

ተስፋዬ ሚደቅሳ መርጋ

ዋሲሁን ሉሌ ወርቅነህ

ገምጋሚ አርታኢዎች

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ትንቢት ግርማ ሀይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

የጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ ይፍሩ

አቀማመጥ እና ስዕል

አንጣጠ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

© የመጽሐፉ ህጋዊ ቅጂ ባለቤት 2014 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

# ምስጋና

የይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ ላደረጉት ከፍተኛ ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉት ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ፣ እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም ሁሌም ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ ለትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ ለቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪ ጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ለአዘጋጅ መምህራን ከዚህ በላይ ስራ የለም በማለት ፍቃድ በመስጠትና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገፅ

መግቢያ

ምዕራፍ አንድ

የአካባቢ ጥበቃ------------------------------------------------------------1

ምዕራፍ ሁለት

የመንገድ ደህንነት-----------------------------------------------------11

ምዕራፍ ሦስት

መረዳዳት -------------------------------------------------------------23

ምዕራፍ አራት

ስርዓተ ፆታ--------------------------------------------------------------34

ምዕራፍ አምስት

ጉብኝት ----------------------------------------------------------------46

ምዕራፍ ስድስት

ስፖርት------------------------------------------------------------------60

ምዕራፍ ሰባት

ውሃ ----------------------------------------------------------------------74

ምዕራፍ ስምንት

መደራደር -------------------------------------------------------------87

ምዕራፍ ዘጠኝ

መገናኛ ብዙኃን ------------------------------------------------------101

ምዕራፍ አስር

ንግድ ----------------------------------------------------------------115

የቃላት ፍቺዎች

ዋቢ ጽሑፎች

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን ለመጀመሪያ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ የመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ-ትምህርት አካል ነው፡፡

መጽሐፉ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዴት እንደሚማሩ ማለማመድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች አካቷል፡፡

1. ተማሪዎች ስዕሎችን በመመልከትና ተረቶችን ወይም ታሪኮችን በማዳመጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ፡፡
2. ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ታሪክ ወይም ንባብ በሚገባ በማዳመጥ ያዳመጡትን ታሪክ ወይም ምንባብ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ በግልፅ ቋንቋ መናገርና መፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ይችሉ ዘንድ በተከታታይ የመናገርና የመፃፍ ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግ አለባቸው፡፡
3. ተማሪዎች ባዳመጡትና ባነበቡት ፅሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላት ካሉ የሚወክሏቸውን ፍቺ በመፃፍ በተገቢው የቃላት አሰዳደር ስርዓት በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን ይማራሉ፡፡
4. ተማሪዎች በተለመዱና በአዳዲስ ቃላት የተመሰረቱ ዓረፍተነገሮችን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ አብረው መማር አለባቸው፡፡ በዚህም የሚያዳምጡትንና የሚያነቡትን ሃሳብ ይረዳሉ፡፡ የቃላት እውቀታቸውንም በማሳደግ በንግግርና በፅሁፍ ሃሳባቸውን በአግባቡ ይገልፃሉ፡፡
6. ተማሪዎች የተለያዩ ተረቶችን ወይም ታሪኮችንና ሌሎች ፅሁፎችን አንብበው መረዳት ይችሉ ዘንድ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን በተደጋጋሚ በመስራት ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ምክር ለወላጆች

ውድ የተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ልጆቻችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የመምህራን እና የእርስዎ ጥምር እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባት በቤትዎ ውስጥ ልጅዎን ያግዙ፡፡

1. ለልጆችዎ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ታሪኮችን፣ ተረቶችን. . .ይንገሯቸው/ ያንብቡላቸው (እንዲያነቡ አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩላቸው)፡፡
2. ለልጆችዎ የነገሯቸውን/ ያነበቡላቸውን ታሪክ/ ተረት ልጆችዎ መልሰው እንዲተርኩ/ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
3. በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችንና ተግባራትን በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው(ያስረዷቸው)፡፡
4. ልጆችዎ በራሳቸው ተነሳሽነት በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
5. ልጆችዎ መምህራቸው በቤታቸው ተዘጋጅተው በመምጣት በተግባር እንዲያሳዩ የሚሰጧቸውን ተግባራዊ ክንውን መተግበሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች በማሟላት የወላጅነት ግዴታዎትን ይወጡ፡፡

አማርኛ
፬ኛ ክፍል



# ምዕራፍ አንድ
## የአካባቢ ጥበቃ

ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የሚነበብላችሁን ምንባብ በማዳመጥ መልዕክቱን ትናገራላችሁ፡፡
- የቀረበላችሁን ምንባብ በማንበብ ዋና ሃሳቡን ትለያላችሁ፡፡
- ለቃላት አውዳዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- አያያዥ ቃል በመጠቀም ውስብስብ አረፍተነገር ትጽፋላችሁ፡፡

ማዳመጥ

## የአረንጓዴ ቦታዎች ምንነት እና ጠቀሜታ

### ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. ከላይ የቀረበው የምንባብ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?
ለ. ፎቶዎቹን በማየት የተረዳችሁትን ግለጹ?
ሐ. አረንጓዴ ቦታ የምንለው ምን ዓይነት ቦታ ነው?

ሀ."የአረንጓዴ ቦታዎች ምንነት እና ጠቀሜታ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. የከተማ አረንጓዴ ስፍራዎች የሚባሉትን ዘርዝሩ?
2. አረንጓዴ ስፍራዎች ያላቸውን ጠቀሜታዎች ተናገሩ?
3. አረንጓዴ እጽዋት የአየር ብክለትን የሚከላከሉት በምን መንገድ ነው?
4. ምንባቡ ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ወይም ሃሳብ ምንድን ነው?
5. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን አረንጓዴ ቦታዎች ዘርዝሩ?

---

### ቃላት

ለ."የአረንጓዴ ቦታዎች ምንነት እና ጠቀሜታ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ከ"ለ" ስር ተመሳሳያቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. የተሸፈነ | ሀ. ድርሻ |
| 2. ረግረግ | ለ. ማጎልበት |
| 3. ማበልጸግ | ሐ. ውሃ የበዛበት ስፍራ |
| 4. ማስረግ | መ. የተከለለ |
| 5. አስተዋጽኦ | ሠ. ማስገባት |

## ጽሕፈት

### ሐ.የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

1. አፈር
2. ደን
3. አየር
4. ማገዝ

---

## ቃላት

### ሀ.በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት በምሳሌው መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- 1. ዛሬ ጠዋት ትኩስ ሻይ ጠጣሁ፡፡ — የሚያቃጥል
2. የልጁ ጉልበት ገና ትኩስ ነው፡፡ — አፍላ ፣ ጠንካራ

1. ያሬድ ዕቁብ ጣለ፡፡
2. ያሬድ በርሳውን ጣለ፡፡
3. ያሬድ ራሱን ጣለ፡፡
4. በሁለቱ ጓደኛሞች ጠብ ምክንያት የክፍላችን ሰላም ደፈረሰ፡፡
5. ዝናቡ ከመጠን በላይ ስለዘነበ ወንዙ ደፈረሰ፡፡

### ለ.በምሳሌው መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ቀጥተኛ እና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-

| ቃል | ቀጥተኛ ፍቺ | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|
| ንብ | ማር የምትሰራ በራሪ ነፍሳት | ታታሪ |

| ተ.ቁ | ቃል | ቀጥተኛ ፍቺ | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| 1 | አንበሳ | | |
| 2 | ምላጭ | | |
| 3 | እባብ | | |
| 4 | ቆቅ | | |
| 5 | መሰላል | | |
| 6 | በግ | | |

## ሰዋስው

### መስተጻምር

ሀ.በምሳሌው መሰረት በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን መስተጻምሮች በመለየት ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-

ነገ ወይም ከነገ ወዲያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና እንፈተናለን፡፡ ወይም

1. እናቴ መጽሐፍ እና ቦርሳ ገዛችልኝ፡፡
2. ጎበዝ መሆን ስለምፈልግ በርትቼ አጠናለሁ፡፡
3. አያቴ ዛሬ ወይም ነገ ትመጣለች፡፡
4. ሰሚራ ብዙ ጊዜ ማጥናት እና መጫወት ትወዳለች፡፡
5. ብሩክ ከቤቱ እስከ ትምህርትቤት የሚሄደው ከጓደኞቹ ጋር ነው፡፡

## ቃላት

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

1. ለምለም
2. መትከል
3. ጥቅም
4. መውሰድ
5. የተሸፈነ
6. ሙቀት

ሐ.ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ መሰረት መስተጻምሮችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- እና

ሰሚራ እና ሰላማዊት ጓደኛሞች ናቸው፡፡

| ወይም | እስከ | እና |
|---|---|---|
| በ | ከ | ግን |

## ንባብ

## እዩኤል እና አሚራ

### ቅድመ ንባብ

ሀ. ከላይ የቀረበው የምንባብ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?
ለ. ምስሉን በማየት የተረዳችሁትን ግለጹ?
ሐ. የክፍላችሁን ንጽህና ለመጠበቅ ምን ታደርጋላችሁ?
መ. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ከሚገኙ ክበባት መካከል በየትኛው ክበብ ትሳተፋላችሁ?



እዩኤል እና አሚራ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: ሁለቱ ተማሪዎች ጓደኛሞች ሲሆኑ በትምህርት ቤታቸው ካሉት ክበቦች መካከል የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አባላት ናቸው:: እዩኤል እና አሚራ በዕቅዳቸው መሠረት በአካባቢ ጥበቃ ክበብ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመረዳዳት በዓመት ውስጥ ብዙ ተግባራትን አከናውነዋል::

የክፍል ጽዳትን መጠበቅና የትምህርት ቤቱን ግቢ ማስዋብ ከተግባራቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: ከዚህም ባሻገር ከትምህርት ቤት ውጪም በተለያዩ የአካባቢ ጽዳቶች ላይ መሳተፍ የክበቡ ዓብይ ተግባር ነው:: እዩኤል እና አሚራ በክበቡ ተግባራት ላይ በመሣተፍ የሥራ ድርሻቸውን ይወጣሉ:: አሚራ በክበቡ ተጠሪነት፣ እዩኤል ደግሞ በክበቡ ፀሐፊነት ያገለግላሉ:: ሁለቱም የክበቡን አባላት የማስተባበር ልዩ ተሰጥኦ አላቸው:: ክበቡን የሚመሩና የሚያስተባብሩ መምህራንም ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ዓመታዊ ዕቅዶችን ይነድፋሉ::

በዚህም መሰረት ዘወትር አርብ የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አባላት የክፍል ፅዳት ተግባራትን የሚያከናውኑበት ቀን ነው:: እነአሚራ የእለቱን ትምህርት ከተማሩ በኋላ በዕቅዳቸው መሠረት የመማሪያ ክፍላቸውን ለማፅዳት ተዘጋጁ:: በዚህ የፅዳት ቀን የክበቡ አባላት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በመረዳዳትና በመተሳሰብ በፅዳቱ ተግባር ላይ ይሳተፋሉ:: ይህ የሣምንቱ የክፍል የፅዳት ቀን ከሌሎቹ የፅዳት ቀናት ይለያል:: በሌሎቹ ቀናት ተማሪዎች በየተራ ክፍላቸውን በመጥረግና ቆሻሻዎችን በተዘጋጀላቸው ቦታ በመድፋት ያፀዳሉ::

ሀ. የእነ እዩኤል እና አሚራ ክበብ ዓብይ ተግባር ምንድን ነው?
ለ. በመቀጠል እዩኤል እና አሚራ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ምን የሚያከናውኑ ይመስላችኋል?

በዚህ የፅዳት ቀን ተማሪዎቹ ክፍሎቻቸውን መጥረግ ብቻ ሳይሆን የክፍሎችን ግድግዳዎች አጸዱ:: መስታወቶችን ወለወሉ:: ቆሻሻዎችንም በመሰብሰብ ከመምህራን ጋር በመሆን በተገቢው መንገድ አስወገዱ:: በዚህ ዓይነት ሁሉም የመማሪያ ክፍሎች መስታወቶች፣ ግድግዳዎችና ወለሎች በሚገባ ፀዱ:: ወንበሮችና ጠረጴዛዎችም በደንብ እየተደረደሩ ተወለወሉ:: በግድግዳዎችና በመስታወቶች ዙሪያ የነበሩ የሸረሪት ድሮችና አቧራዎች ተራገፉ::

ተማሪዎቹ በሠሯቸው ተግባራት በጣም ተደሰቱ:: ርስበርስ በመረዳዳት በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ተግባራትን በማከናወናቸው ለሌሎች ክበብ አባላት አርአያነታቸውን አስመሰከሩ:: ከዚያም የሳምንቱ የትምህርት ቀን ማብቂያ በመሆኑ ሰኞ ለመገናኘት የስንብት ሰላምታ ተለዋውጠው ተለያዩ::

(በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር፤ በ2009 ዓ.ም፤ አጋዥ መጽሀፍ ለንባብ ትምህርት ፤ ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተስማምቶ የቀረበ::)

---

ሀ. "እዩኤል እና አሚራ" በሚል ርዕስ በቀረበላችሁ ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልሱ::

1. እዩኤል እና አሚራ የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው?
2. እዩኤል እና አሚራ በትምህርት ቤታቸው የሚሳተፉበት ክበብ ምን ይባላል?
3. ተማሪዎቹ የሚያጸዷቸውን ስፍራዎች ዘርዝሩ?
4. ተማሪዎቹ በሌሎች ቀናቶች የክፍላቸውን ንጽህና እንዴት ይጠብቃሉ?
5. እናንተስ ከአሁን በኋላ በትምህርት ቤታችሁ እና በአካባቢያችሁ ምን ለማድረግ አሰባችሁ?

---

### ጽሕፈት

ለ.እዩኤል እና አሚራ በሚል ርዕስ የቀረበላችሁ ምንባብ ዋና መልዕክት በራሳችሁ አገላለጽ በአራት አረፍተነገሮች ጻፉ።

### ቃላት

ሐ.ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ጻፉ።

1. አርዓያ
2. መሰብሰብ
3. ማስዋብ
4. አብይ
5. ስፍራ
6. ማብቂያ
7. ተለዋወጡ
8. በተገቢው

### ሰዋስው

**የዓረፍተ ነገር ምንነት**

ዓረፍተ ነገር ማለት የተሟላ መልዕክት ማስተላለፍ የሚችል እና በስርዓት የተደረደሩ ቃላት ስብስብ ነው።

ምሳሌ:-

ሀ. የአማርኛ ጽሑፎችን በሚገባ አነባለሁ። (ይህ ዓረፍተ ነገር ነው ምክንያቱም ቃላቱ በትክክለኛው ቅደም ተከተል ተደርድረዋል፤ ሙሉ ሃሳብም ያስተላልፋሉ።)

ለ. እህቴ ጽሑፍ (ይህ ዓረፍተ ነገር አይደለም ምክንያቱም ሃሳቡ አልተሟላም።)

ሐ. የዚህ ክፍል ተማሪዎች ጎበዞች ናቸው። (ይህ ዓረፍተ ነገር ነው ምክንያቱም ቃላቱ በትክክለኛው ቅደም ተከተል ተደርድረዋል፤ ሙሉ ሃሳብም ያስተላላፋሉ።)

ሀ. የሚከተሉት ጽሑፎች ዓረፍተ ነገር መሆናቸውን ወይንም ዓረፍተ ነገር አለመሆናቸውን በመለየት ጻፉ።

1. እርስ በእርስ መረዳዳት የሚያኮራ ባህል ነው
2. የአድዋ ጦርነት በ1888 ዓ.ም
3. ባህላዊ አልባሳቶቻችን የማንነታችን መገለጫዎች ናቸው
4. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በርካታ ብሔረሰቦች በአንድነት ይኖራሉ
5. ሕጻናትን ለጉልበት ብዝበዛ መዳረግ
6. ግብር መገበር የዜግነት

## የዓረፍ ተነገር ዓይነቶች

ዓረፍተ ነገሮች በውስጣቸው ከሚይዙት ሃሳብ ብዛት አኳያ በሁለት ምድብ ይከፈላሉ እነሱም ነጠላ ዓረፍተ ነገር እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ናቸው፡፡

1. ነጠላ ዓረፍተ ነገር ፡- የሚባለው ዓረፍተ ነገሩ አንድ ሃሳብን ብቻ የሚያስተላላፍ የዓረፍተ ነገር ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. የኮሮና ቫይረስ በአለም ላይ ተሰራጨ ፡፡
ለ. ሃያት ወደ ትምህርት ቤት ሄደች ፡፡
ሐ. ሜሮን መፅሐፍ ገዛች ፡፡

2. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ፡- የሚባለው ደግሞ  በዓረፍተ ነገሩ ዉስጥ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ተያያዥነተት ያላቸውን ሃሳቦችን የሚይዝ የዓረፍተነገር ዓይነት ነው ፡፡

ምሳሌ ፡-ሀ. ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ተላላፊ በሽታ ነው ስለዚህ መጠንቀቅ አለብን፡፡
ለ. የሱፍ ኳስ መጫወት ይችላል ነገር ግን ብስክሌት መንዳት አይችልም፡፡
ሐ. ትህትና መጽሀፍ ገዛች እና ለወንድሟ ሰጠችው፡፡

---

**ለ.** የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ ዓረፍተ ነገር ወይም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መሆናቸውን በመለየት ጻፉ፡፡

1. ምግቡ ብዙ ዓይነት ነው ይሁን እንጂ አንዱም አይጣፍጥም፡፡
2. ዘወትር አካባቢያችንን እናጸዳለን፡፡
3. በርትታ አጠናች ስለዚህ ጥሩ ውጤት አስመዘገበች፡፡
4. ሰዓዳ እርሳሷን አልያዘችም ነገርግን ትምህርትቤት ሄዳለች፡፡
5. ሮቤል በጠዋት ወደ ትምህርትቤት ሄደ፡፡
6. ኢትዮጵያን ከልቤ እወዳለሁ፡፡

---

**ሐ.ወደረኛ መስተጻምሮችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፡-  እኔ እና ጓደኛዬ በጋራ እናጠናለን፡፡

የሚከተሉትን ጥገኛ መስተጻምሮች በክፍት ቦታው ላይ በማስገባት ው·ዓረፍተነገሩን  አሟሉ፡፡

| እየ | ስለ | በ | ከ |
|---|---|---|---|

1. ዳዊት ብዙ ጊዜ ______ሚያነብ ጥሩ ውጤት አስመዘገበ፡፡
2. በጠዋት መነሳት ______ፈለኩ እንቅልፍ ይጥለኛል፡፡
3. ዛሬ አባቴ ____________ መጣ መዝናኛ ቦታ ይወስደኛል፡
4. መንገዱ ስለማይመች _____መኪና አንሄድም፡፡

## አያያዥ ቃላት

አያያዥ ቃላት የምንላቸው ቃልን ከቃል ፣ ሐረግን ከሐረግ ፣ ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር በማያያዝ አንድን ሐሳብ ከሌላ ሐሳብ ጋር በማዋሀድ የሐሳብ ፍሰቱ የተጠበቀ እንዲሆን የሚያገለግሉ ናቸው። አያያዥ ቃላት ከምንላቸው ውስጥ ፡-

ስለዚህ፣ ነገር ግን፣ በመሆኑም፣ ይሁን እንጂ፣ የሆነው ሆኖ፣ ምክንያቱም፣ ስለሆነም፣ . . .

ምሳሌ፡-

ሀ.አዲስ አበባ ብዙ የሚጎበኙ ቦታዎች አሉ።
ለ.አንዱንም አልጎበኘም።
→ አዲስ አበባ ብዙ የሚጎበኙ ቦታዎች አሉ፤ ይሁን እንጂ አንዱን አልጎበኘም።

ሀ.ሰናይት ዘወትር ታነባለች ።
ለ.ሰናይት ጥሩ ውጤት አመጣች።
→ ሰናይት ዘወትር ታነባለች፤ በመሆኑም ጥሩ ውጤት አመጣች።

---

### ሠ.የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ጻፉ።

1. ነገር ግን
2. ስለዚህ
3. ምክንያቱም
4. በመሆኑም
5. ስለሆነም

### ለ. የሚከተሉትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ወደ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በመቀየር ፃፉ ።

1. ሔኖክ ቁርሱን በላ።
   ሔኖክ የተመገበው ምግብ አልተስማማውም ።
2. ማርታ ገበያ ሄደች ።
   ማርታ ብርቱካን ገዛች ።
3. የሒሳብ ትምህርት ይከብደኛል ።
   የሂሳብ ትምህርት ከማጥናት አልቆጠብም ።
4. ሶፊያ ከክፍሏ አንደኛ ወጣች ።
   ሶፊያ ተሸላሚ ሆነች ።

## የምዕራፍ አንድ የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቃላት አውዳዊ እና ፍካሬዊ ፍቺ ማለት ምን ማለት ነው? በምሳሌ አብራሩ?
2. የመስተጻምር ዓይነቶች ____________እና_____________ይባላሉ፡፡
3. ስለዚህ

   ቢሆንም

   ነገር ግን     በሚሉት አያያዥ ቃለት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡
4. ማገዝ

   ማስረግ

   መጠን

   ዕቅድ  ለሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ስጡ፡፡
5. ማስዋብ

   መጉዳት

   ማብቂያ    ለሚሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ፡፡
6. ቋንጣ

   ዱባ      ለሚሉት ቃላት ቀጥተኛ እና  ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡
7. ነጠላ እና ውስብስብ ዓፍተነገሮችን ጻፉ፡፡


# ምዕራፍ ሁለት
## የመንገድ ደህንነት

ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ስለ መንገድ ደህንነት መዝሙር አዳምጣችሁ ትዘምራላችሁ፤
- የሚሰጣችሁን አንቀጽ አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፤
- ቃላትን ከተጨባጭ ህይወታችሁ ጋር ታዛምዳላችሁ፤
- አያያዥ ቃል በመጠቀም አረፍተነገር ትመሰርታላችሁ፤

## ማዳመጥ

### "ልጆች ተጠንቀቁ"





**ቅድመ ማዳመጥ**

ሀ. ከላይ የቀረበው ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?
ለ. ፎቶዎቹን በማየት የተረዳችሁትን ግለጹ?
ሐ. የመንገድ ላይ ጥንቃቄ ማለት ምን ማለት ነው?
መ. ስለመንገድ አጠቃቀም የምታውቁትን ግለጹ?

---

ሀ. "ልጆች ተጠንቀቁ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት መዝሙር መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. የአስፓልት መንገድ ስንሻገር ማቋረጥ ያለብን በምን ዓይነት ቦታ ላይ ነው?
2. አረንጓዴ መብራት ሲበራ ተራው የማን ነው?
3. ቀይ መብራት ሲበራ ተራው የማን ነው?
4. በመንገድ ላይ ስንጓዝ የትኛውን አቅጣጫ መከተል አለብን?

### ቃላት

ለ "ልጆች ተጠንቀቁ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት መዝሙር መሠረት ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

1. ልጆች
2. ሁሉንም
3. ሲሻገሩ
4. አያለሁ
5. ስሄድ

---

### ጽሕፈት

ሀ."ልጆች ተጠንቀቁ" በሚል ርዕስ ካዳመጣችሁት መዝሙር የተረዳችሁትን ሃሳብ በአራት አረፍተ ነገር ጻፉ።

---

### ቃላት

ሀ.በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡

1. መንገድ ስንጓዝ የግራ ጠርዝ መያዝ ይኖርብናል።
2. በአካባቢያችን በርካታ መኪናዎች ይንቀሳቀሳሉ።
3. በሳምንት አንድ ቀን በብስክሌት እሄዳለሁ።
4. አሽከርካሪዎች ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።
5. በአዲስ አበባ ረጃጅም ጎዳናዎች አሉ።

---

ሊ ለሚከተሉት ዝርዝር ሃሳቦች በምሳሌው መሰረት መልስ መሆን የሚችሉ ቃላትን ለመመስረት በተሰጠው የአቅጣጫ መጠቆሚያ መሰረት አንድ፤ አንድ ፊደላትን ወደ ጎን እና ወደታች በመልስ መስጫ ሳጥኑ ውስጥ ጻፉ።

## ወደ ጎን

| ቁጥር | መግለጫ |
|---|---|
| 1 | ለአገር እና ለወገን መልካም ተግባርን ያከናወነ ሰው፤ |
| 3 | አበባ የምትቀስም እና በታታሪነት የምትጠቀስ ነፍሳት፤ |
| 4 | ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሰራ የአገራችን ጥንታዊ ሃውልት፤ |
| 7 | ከመሬት ውስጥ የሚገኝ የእጽዋት ክፍል፤ |
| 8 | ንጽህናን ለመጠበቂያነት የሚያገለግል አረፋ ያለው ጠጣር ቁስ፤ |
| 9 | በምንተኛበት ጊዜ ለጭንቅላት መደገፊያነት የሚያገለግል፤ |

## ወደ ታች

| ቁጥር | መግለጫ |
|---|---|
| 2 | ግንብ የመገንባት ሙያ ያለው ሰው፤ |
| 4 | የእናት ወይም የአባት እህት ፤ |
| 5 | ባለስድስት አውታር ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ፤ |
| 6 | በአንድ በኩል የተቦረቦረና የተለያዩ ነገሮች ተጨምረውበት የሚወቀጥበት የቤት ዕቃ፤ |
| 10 | በሁለቱም እግሮቻችን በማስገባት እግሮቻችንን በሙሉ የሚሸፍን የልብስ ዓይነት፤ |

## የመልስ መስጫ ሳጥን

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 ግ | | 4 አ | 5 | 10 ሱ | | | |
| | 3 ን | | | | | 8 | 6 ሙ | |
| | | | 7 | | | | | |
| | | | 9 | | ስ | | | |

## ንባብ

# የሾፌሩ ታሪክ

### ቅድመ ንባብ

ሀ. ከላይ የቀረበው ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?
ለ. ፎቶውን በማየት የተረዳችሁትን ግለጹ?
ሐ. የትራፊክ አደጋ በምን ምክንያት የሚደርስ ይመስላችኋል?



የ38 ዓመት ጎልማሳ ነኝ። ድፍን አስር አመታትን በታክሲ ሾፌርነት አገልግያለሁ፡ ተወልጄ ያደኩት በአዲስ አበባ ከተማ ነው። የአንደኛ እና የሁለተኛ ደርጃ ትምህርቴን በአቃራቢያዬ በሚገኙ ትምህርትቤቶች ተምሬአለሁ። በትምህርቴ በጣም ጎበዝ ባልባልም ከሠነፎች ተርታ የምመደብ አልነበርኩም። ለቤተሰቦቼ ብቸኛ ልጃቸው እኔ ስለሆንኩ ቤተሰቦቼ የሚያገኙትን አነስተኛ ገቢ ለመጨመርና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሯችንን ለማሳደግ በማሰብ የመንጃ ፈቃድ አውጥቼ በታክሲ ሾፌርነት እየሰራሁ የእራሴንና የቤተሰቤን ገቢ መደጎም ጀመርኩ። ስራዬ የታክሲ ሾፌር በመሆኑ በየቀኑ ከበርካታ ሰዎች ጋር የመተዋወቅ እድል ፈጠረልኝ። መጀመሪያ አካባቢ ጊዜዬን በሙሉ ተጠቅሜ ስለምሰራ ዳጎስ ያለ ገቢ ማግኘት ቻልኩ።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን ሰበባሰበብ እየፈጠርኩ መጥፎ ጠባዮችን መላመድ ጀመርኩ። በተለያየ ጊዜ ወደ ጫት ቤት በመሄድ ጫት መቃም ለመድኩ። ቀስ በቀስ የጫት ቃሚ ጓደኞች በመያዝ ከምሳ ሰአት በኋላ ስራ ትቼ የምዉለው ጫት ቤት ነበር፡ አስራአንድ ሰዓት ሲሆን የሰራተኞች የስራ መውጫ ሰዓት ስለሆነ ወደስራዬ እሄዳለሁ። ምሽት ግን ወደቤት መግባት ሲገባኝ እንቅልፍ አይወስደኝም በሚል ሰበብ ወደመጠጥ ቤት እሄዳለሁ። አንድ ቤት መጠጣት እጀምርና በሞቅታ ሳላውቀው ወደተለያዩ ቤቶች እየተዟዟርኩ እስክሰክር ስጠጣ አመሻለሁ።

ሀ. ባለታሪኩ በትምህርቱ ምን ዓይነት ተማሪ ነበር?
ለ. ባለታሪኩ መጠጥ በመጠጣቱ ምን የሚያጋጥመው ይመስላችኋል?

አንድ ቀን ግን እንደተለመደው ከስራ መልስ ወደመጠጥ ቤት ስገባ የልጅነት የትምህርት ቤት ጓደኛዬን ሲጠጣ አገኘሁት፡፡ ከጓደኛዬ ጋር የተገናኘነው ከረጅም ጊዜ በኋላ ስለሆነ ሞቅ ያለ ሰላምታ ከተቀያየርንና አብረን ስንጠጣ ካመሸን በኋላ ጓደኛዬን ወደቤቱ ለማድረስ ታክሲዬን አስነስቼ ከመጠን በላይ በሆነ ፍጥነት እየነዳሁ ጉዟችንን ቀጠልን፡፡ ከመጠን በላይ ጠጥተንና ሰክረን ስለነበር ፍጥነታችንን መቀነስ ሲገባን ይበልጥ እየጨመርን፣ በአነዳዴ እየሳቅን እና ሙዚቃ ከፍ አርገን እያዳመጥን ስንሄድ ድንገት ከቆመ ገልባጭ መኪና ጋር ተላተምን፡፡

ከወር በኋላ ራሴን በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ አገኘሁት፡፡ እንደነቃሁ የጓደኛዬ ህይወት ሳይመለስ እስከ ወዲያኛው ማሸለቡን ነገሩኝ፡፡ እኔም የቀኝ የሰውነት ክፍሌን ማንቀሳቀስ አቅቶኝ የአልጋ ቁራኛ ለመሆን ተገደድኩ፡፡

ጠጥቼ በማሽከርከሬ እና የትራፊክ ሕጎችን ባለማክበሬ ለወላጆቼ ተጨማሪ ሸክም ሆንኩ፡፡ በየቀኑ እንደእኔ የትራፊክ ደንብን ባለማክብርና ጠጥቶ በማሽከርከር የሚጠፋውን የሰው ህይወት፣ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት ሳስብ አሽከርካሪዎች በመጠንቀቀቅ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ከእኔ ተማሩ እላለሁ፡፡

---

ሀ."የሾፌሩ ታሪክ" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ባለታሪኩ ስንት ዓመቱ ነው?
2. ባለታሪኩ የምን ሾፌር ነበር?
3. አደጋው በደረሰበት ወቅት የሾፌሩ ጓደኛ የተቀመጠው በየት አቅጣጫ ነበር? ለምን?
4. የባለታሪኩ የኑሮ ደረጃ በምን ዓይነት ሁኔታ ቀጠለ?
5. በምንባቡ መሰረት ሾፌሩ የመኪና አደጋ የደረሰበት ለምን ይመስላችኋል?

## ቃላት

ሀ.በምንባቡ መሰረት በ" ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | " ለ" |
|---|---|
| 1. መደጎም | ሀ.ሳይታሰብ |
| 2. ሰበባሰበብ | ለ.መርዳት |
| 3. በድንገት | ሐ.ምድብ |
| 4. ተላተምን | መ.ምክንያት |
| 5. ተርታ | ሠ.ተጋጨን |

ለ. ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| 1. አሳዛኝ | 3. ዝቅተኛ | 5. መጥፎ |
| 2. መቀነስ | 4. ጎበዝ | 6. ገቢ |

---

## መናገር

ሀ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ የመወያያ ርዕስ መሰረት በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ የውይይታችሁን ሃሳብ አካፍሉ።

---

## አቀላጥፎ ማንበብ

### አንበሳ

አንበሳ በድመት ዘር ውስጥ ካሉት እንስሳት ግርማ ሞገስ ያለው፣ ኃይለኛና አስፈሪ ከሩቅ ሲመለከቱት ደስ የሚል አውሬ ነው። ቁመቱ እስከ አንድ ሜትር ርዝመቱ (ጅራቱን ሳይጨምር) ሁለት ሜትር ይደርሳል፤ ክብደቱ እስከ 236 ኪሎ ይመዝናል። ሆዱ ላይ ትንሽ ነጣ ከማለቱ በቀር ጸጉሩ ወርቃማ ቢጫ ነው። ሲያረጅ ጎፈሩ ይጠቁራል። ጅራቱ ረጅም ጭራው አጭርና ጥቁር ነው። ሴቷ አንበሳ ከወንዱ አነስ ብላ ዘለግ ያለች ነች፤ ጎፈር የላትም። የአንበሳ የእርግዝና ወቅት አራት ወር ሲሆን በአንድ ጊዜ ከ2 እስከ 4 ደቦሎችን ትወልዳለች። አንበሳ እስከ 25 አመት እድሜ ይኖራል።

(ለማ ጉያ፣1995፣ ያላስተማሪ የሥዕል ትምህርት መማሪያ ፣ ገጽ 84፤ ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተደርጎ የቀረበ )

---


## ቃላት

**ሀ.በየሳጥኑ ዙሪያ ላሉት ቃላት ተመሳሳይ የሚሆነውን ቃል ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በመምረጥ ሳጥኑን አሟሉ፡፡**


### የተሰጡ አማራጭ ቃላት

| ማጽዳት | ረጅም | ደግነት | ማሰብ |
|---|---|---|---|


1.





2.




3.




4.



### ሰዋስው

### ሀ.ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በመግባት ሃሳቦችን ሊያሟሉ የሚችሉ አያያዥ ቃላትን ምረጡ፡፡

1. ሴቶችም______________ወንዶች እኩል የሆነ መብት አላቸው፡፡

   ሀ. ሲሆንም ለ.ነገርግን ሐ. ሆኑ መ. ስለዚህ

2. ህንፃው ተሰርቶ ከተጠናቀቀ ቆይቷል፤_____________ እስከ አሁን አገልግሎት መስጠት አልጀመረም፡፡

   ሀ. ነገርግን ለ. ወይም ሐ. ደግሞ መ. ሆነ

3. አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጌአለሁ_________________________ፈተናውን በድል አጠናቅቃለሁ፡፡

   ሀ. ነገርግን ለ. ወይም ሐ. ሆኑ መ. ስለዚህ

4. በሚቀጥለው ሳምንት_________________አስራ አምስት ቀን ወደ ላሊበላ መሄዴ አይቀርም፡፡

   ሀ.ሲሆንም ለ. ወይም ሐ. ስለዚህ መ. ደግሞ

5. ማስረሻ የእግር ኳስ ተጫዋች ሲሆን ፋጡማ_____________ሯጭ ናት፡፡

   ሀ. ደግሞ ለ. ስለዚህ ሐ. ወይም መ. ነገርግን

---

### ለ.የሚከተሉትን ቃላት በባዶ በታዎች ውስጥ በማስገባት ዓረፍተነገሮቹን አሟሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጨዋታዎች | ማስተማር | ማታ | መንገዶች |
| መማር | እንዳይሰደዱ | አጠገብ | ክብር |

1. ዘወትር__________________ትምህርቴን አጠናለሁ፡፡
2. ትምህርታችንን በትጋት_______________አለብን፡፡
3. ልጆች የሚጫወቱት በርካታ ____________________አሉ፡፡
4. የዱር እንስሳት____________አካባቢያችንን መንከባከብ አለብን፡፡
5. የኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ_____________በማወቅ ጥንቃቄ እናድርግ፡፡

6. የምናውቀውን ለማያወቁት ________________እንችላለን፡፡

7. ለወላጆቻችን ተገቢውን _______________መስጠት አለብን፡፡

---

## ጽሕፈት

### ሀ.ከሚከተለው ጽሁፍ ውስጥ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ብቻ በመለየት ጻፉ፡፡

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ናት፡፡ በከተማዋ ስለመንገድ ደህንነት በተመለከተ በተለያየ መንገድ ትምህርት ይሰጣል፤ ይሁን እንጂ በርካታ የትራፊክ አደጋዎች ያጋጥማሉ፡፡ ለትራፊክ አደጋ እንደመንስኤ ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የመንገድ ህጎችን አለማወቅ ነው፡፡ አሽከርካሪዎችና እግረኞች በሙሉ የመንገድ አጠቃቀም ህጎችን ማወቅ አለባቸው፡፡ የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ለምፍጠር ባለድርሻ አካላት ሁሉን አቀፍ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፤ ቢሆንም ህብረተሰቡ የግንዛቤ ለውጥ አላመጣም፡፡

### ለ. በምሳሌው መሰረት የተዘበራረቁትን ቃላት ቅደም ተከተል በማስተካከል የተሟላ ሃሳብ የሚያስተላልፍ ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ንጽህና / የክፍላችንን / እንጠብቃለን / እኛ

- እኛ የክፍላችንን ንጽህና እንጠብቃለን፡፡

1. እኔ / ነኝ / ክፍል / ተማሪ / የአራተኛ
2. ባህላችንን / የማክበር / እንግዳ / ልናዳብር / ይገባል
3. ጳጉሜ / ነው / የአመቱ / ወር / የመጨረሻ
4. ምቹ / መንገዱ / አይደለም / ለመኪና
5. ረጅሙ / በአለማችን / ወንዝ / ነው / አባይ

---

ሐ. በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ወደረኛ መስተጻምሮች በመጠቀም በእያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ፡፡

| | |
|---|---|
| እና | ወይም |

ምሳሌ፡-

1. ኸይሩ እና ሃና ዘወትር ያጠናሉ፤ በመሆኑም ጥሩ ውጤት ማመዝገባቸው አይቀርም፡፡
2. ነገ ወይም ከነገወዲያ የሩጫ ውድድር አለብን፤ ስለዚህ የስፖርት ልብሶቻችንን ማምጣት አለብን፡፡

## የምዕራፍ ሁለት የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ ማለት ምን ማለት ነው? በምሳሌ አብራሩ?
2. ወደረኛ መስተጻምሮችን በመጠቀም ውስብስብ ዓፍተነገሮችን መስርቱ፡፡
3. አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡
4. የንባብ ችሎታችሁን ለማዳበር መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት የቀረበላችሁን ምንባብ ተለማመዱ፤ ለክፍል ጓደኞቻችሁም ተራ በተራ አንብቡ፡፡

### ማርስ

ከቅርብ ፕላኔቶች መሀል ከፀሀይ ርቃ የምትገኘው ማርስ ናት፡፡ የጥንት ሮማዊያን ማርስ ብለው የሰየሟት በጦር አምላካቸው ስም ነው፡፡ ማርስ ከመሬት ጋር ብትመሳሰልም ልዩነቶች ግን አሏት፡፡ ለምሳሌ ማርስ ከመሬት ታንሳለች፡፡ መሬትን አንድ አስረኛ ነው የምታክለው፡፡ማርስ ቀላ ያለች ስተሆን፣ዋልታወቿ ነጣ ያሉ ናቸው፡፡

ማርስ ላይ ሸለቆዎች፣ ሜዳዎችና ተራራማ ቦታዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ማርስ ወገብ አካባቢ ትልቅ ሸለቆ ይገኛል፡፡ የዚህ ሸለቆ ርዝማኔ 5 ሺህ ኪሎሜትር ሲሆን፣ የጎን ስፋቱ 100 ኪሎ ሜትር ነው፡፡ ጥልቀቱም 10 ኪሎሜትር ይሆናል፡፡ የማርስ ትልቁ ተራራ ኦሊምፐስ በመባል ይታወቃል፡፡ ከፍታውም 25 ኪሎሜትር ይሆናል፡፡ በመሬት ላይ የሚገኘው ትልቁ ተራራ ኤቨረስት በመባል ይታወቃል፡፡ በማርስ ገጽታ ሌላም የሚታይ ነገር አለ፡፡ እሱም የወንዝ መውረጃ የመሰለ ጉድጓድ፤ ይህ የወንዝ መውረጃ ጎደጓዳማ ስፍራ በአንድ ወቅት ማርስ ላይ ውሀ እነደነበር ያስረዳል በማለት የስነፈለክ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡

ማርስ ከባቢ አየር አላት፡፡ ከባቢ አየሩዋም እነደ ቬነስ ከባቢ አየር ጥቅጥቅ ያለ ሳይሆን በጣም ስስ ነው፡፡ የተሰራውም በአብዛኛው ካርቦንዳይኦክሳይድ ከተባለው ጋዝ ነው፡፡ ጥቂት ይሁኑ እንጅ ናይትሮጂን ፣ኦክስጅን እና ውሀ ይገኙበታል፡፡ በይዘትም ከመቶ 95 እጁ ካርቦንዳይኦክሳይድ ነው፡፡ የሚዘዋወር ጥቂት ደመናም አለ፡፡ ሆኖም ይህ ደመና ዝናብ የማዝነብ አቅም ያለው አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት በማርስ ላይ ዝናብ አይዘንብም፡፡ሆኖም ብዙውን ጊዜ የማርስን ሸለቆዎች በጭጋግ ተሸፍነው ነው የምናያቸው፡፡

ማርስ ከሌሎች ቅርብ ፕላኔቶች ይበልጥ ከፀሐይ፣ ከሜርኩሪ፣ከቬነስና ከመሬት የበለጠ ትቀዘቅዛለች፡፡የማርስ ሙቅት ቀን ከ0$^{0}$c ጥቂት ከፍ ሲል፣ በምሽት ወቅት ከዜሮ በታች 20$^{0}$c ይወርዳል፡፡ይህም ቅዝቃዜ መሬት ላይ በብዙ ቦታዎች የሚታይ አይደለም፡፡

ማርስ ሁለት ትናንሽ ጭፍራዎች አሉዋት፡፡ እነርሱም ፎቦስና ዴይሞስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

( ምንጪ:-እሸቱ አሰፋ፤2000፤ፕላኔቶችናሌሎች የሰማይት አካለት፤ገጽ 51-54)

5. "ማርስ" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የተረዳችሁትን መልዕክት በአራት ዓረፍተ ነገር ጻፉ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት
## መረዳዳት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ያዳመጣችሁትን ምንባብ መልዕክት ትናገራላችሁ፤
- በክፍል ደረጃችሁ ያነበባችሁትን ጽሁፍ ዋና ሃሳብ ትለያላችሁ፤
- ቅጥያዎችን ተጠቅማችሁ አረፍተነገር ትጽፋላችሁ፤
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅማችሁ ነጠላ እና ውስብስብ አረፍተነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### እህትማማቾቹ



### ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. ከላይ የቀረበው ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?
ለ. ምስሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ግለጹ?
ሐ. መረዳዳት ከየት ይጀምራል?

ሀ."እህትማማቾቹ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ቤተልሄም ፍቅርን የምትበልጣት በስንት ዓመት ነው?
2. ቤተልሔም ፍቅርን "አንቺ እኮ እስትንፋሴ ነሽ፡፡" ስትል ምን ለማለት ፈልጋ ነው?
3. ፍቅር ወደበሩ የሮጠችው ለምንድን ነው ?
4. እናንተ በቤት ውስጥ በአቅማችሁ ምን ምን ስራዎችን ትሰራላችሁ ?

---

## ቃላት

**ሀ.“እህትማማቾቹ” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በ “ሀ” ረድፍ ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከ “ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።**

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. መብለጥ | ሀ.ልዩነት |
| 2. አንድነት | ለ. ቆሸሸ |
| 3. ፍቅር | ሐ. መዘንጋት |
| 4. ጸድቶ | መ. ማነስ |
| 5. ማስተዋል | ሠ. ጥላቻ |

---

**ለ.“እህትማማቾቹ” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳያቸው ጻፉ።**

ምሳሌ:-

ቤቱን በተቻለኝ አቅም በዚህ መልኩ አዘጋጀሁት። = አስተካከልኩት

1. ፍቅር ቤቱን ወልውላ ሶፋውን እና ጠረጴዛዎችን አስተካከለችው።
2. ወዲያውኑ የግቢያቸው በር ለመክፈት ወደበሩ ተፈተለከች።
3. ቤተልሄም በታናሽ እህቷ በመገረም “አንቺ እኮ እስትንፋሴ ነሽ” አለቻት።
4. ቤተልሄም የራሷን የቤት ስራ ከጨረሰች በኋላ ፍቅርን ታስጠናታለች።
5. ቤቱን ለማስተካከል እየተቻኮለች ወደ ሳሎን ገባች።

---

## ጽሕፈት

**ሀ.“እህትማማቾቹ” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉት አገላለጾች ምን ማለት እንደሆኑ አብራሩ።**

1. ተሰናብተው ወጡ
2. ማዕድቤት
3. ልዩ ውበት አጎናፀፈችው
4. እንደመስከረም ሰማይ

---

ለ.“እህትማማቾቹ” በሚል ርዕስ ካዳመጣችሁት ምንባብ የተረዳችሁትን ሃሳብ በአራት አረፍተነገርሮች ጻፉ፡፡

ሐ.በምሳሌው መሰረት ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፤በመቀጠል በሰጣችሁት ፍቺ ዓረፍተነገሮች መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሃሴት = ተመሳሳይ ፍቺ፡- ደስታ

ተቃራኒ ፍቺ፡- ሐዘን

ሀ. ሁሌም በቤታችን ትልቅ ደስታ አለ፡፡

ለ. በባህላችን ሐዘን ሲያጋጥም ነጠላ ተዘቅዝቆ ይለበሳል፡፡

1. ትልቅ
2. አጭር
3. ቆሸሸ
4. ፈጣን

## ንባብ

### የመረዳዳት ጥግ



### ቅድመ ንባብ

*ሀ. የመረዳዳት ጥግ የሚለው የንባብ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል፡፡*
*ለ. ከላይ የምትመለከቱት ፎቶግራፍ የማን ነው?*
*ሐ. መረዳዳት ማለት ምን ማለት ነው?*
*መ. እናንተ ሰውን ረድታችሁ ታውቃላችሁ? ምን በማድረግ?*

ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና በቀድሞው ሸዋ ክፍለሃገር በሰላሌ አውራጃ ልዩ ስሙ ሸበል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተወለዱ፡፡ ወይዘሮ አበበች የአብራካቸው ክፋይ የሆነ አንድም ልጅ የላቸውም፡፡ ወይዘሮ አበበች አጠር ያሉ የቀይ ዳማ ሲሆኑ ደግነት፣ መንፈሳዊነት፣ ሩህሩህነትና አዛኝነት ከፊታቸው ላይ ይነበባል፡፡ በተለይ ትህትናቸው ከልብ ነው፡፡
የወይዘሮ አበበችን የህይወት አቅጣጫ የለወጠው የወሎ ጉዟቸው ነበር፡፡ መስከረም 14 ቀን 1972 ዓ.ም ግሸን ማርያምን ሊያነግሱ ወደ ወሎ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ወደ ግሸን የተጓዙት ወይዘሮ አበበች ወሎ ተከስቶ በነበረው ድርቅ ምክንያት ባዩትና ባስተዋሉት ነገር መንፈሳቸው ተነክቶ የሙት እናቷን ጡት እየጠባች ያገኟትን ህፃን ይዘው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡

*ሀ. ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና የት ተወለዱ?*
*ለ. ከዚህ በኋላ ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?*

ከዚህ በኋላ ከትዳራቸውና ከዘመዶቻቸው ይልቅ ዘመድ አልባና ምንም ደጋፊ የሌላቸውን ልጆች መረጡ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ 21 ህፃናትን ይዘው መኖር ሲጀምሩ፣ የ21 ህፃናትን ጉሮሮ ለመድፈን፣ አልባሳትን ለማሟላት በመጀመሪያ የነበሯቸውን ልዩ ልዩ ወርቅ አና ጌጣጌጦች ሸጡ፡፡ በገንዘቡ እህል ሸምተው እንጀራና ዳቦ እየጋገሩ፣ ቆሎ እየቆሉ መሸጡን ተያያዙት፡፡ በሚገኘው ትርፍም ልጆቻቸውን መመገብና ማልበስ ቻሉ፡፡

በጥቂት ህፃናት የተጀመረው ሰብዓዊ ተግባር በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ አድጎ በብዙ ማህበረሰባዊ እድገትና ልማት ውስጥ ተስፋፍቶ ማህበረሰቡን ለለውጥና ለእድገት በማንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ የድርጅቱ መጠሪያ በአሁኑ ጊዜ አበበች ጎበና የህፃናት እንክብካቤና ልማት ማህበር በመባል ይታወቃል፡፡

ወይዘሮ አበበች ጎበና ለሃገርና ለወገን ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ የጅማ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷቸዋል፡፡ ድርጅታቸው ለሰብዓዊ ድጋፍና እንክብካቤ ላደረገው አስተዋጽኦ በየጊዜው ከተለያዩ አለማቀፍና አገር አቀፍ ድርጅቶች በርካታ ዋንጫዎችንና የምስክር ወረቀቶችን አግኝቷል፡፡ ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና በ85 ዓታቸው ሰኔ 27 ቀን 2013 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ቀን ድረስ ድርጅቱን በዋና ስራ አስኪያጅነት ሲመሩ ነበር፡፡

ምንጭ፡- ሺበሺ ለማ(2007ዓ.ም)፤ አርዓያዎቹ- የ12ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መጽሀፍ ለክፍል ደረጃው እንዲያመች ተደርጎ ተሸሽሎ የቀረበ

## ሀ."የመረዳዳት ጥግ " በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።

1. አበበች ጎበና የት አካባቢ ተወለዱ?
2. ከትዳራቸውና ከዘመዶቻቸው ይልቅ ምንም ደጋፊ የሌላቸውን ልጆች ለምን መረጡ?
3. ለአገርና ለወገን ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ ምን አገኙ?

## ለ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጡ።

1. የወይዘሮ አበበችን የህይወት አቅጣጫ የቀየረው ምን ነበር?
   ሀ. የቤተሰባቸው ፍቅር ለ. የወሎ ጉዟቸው
   ሐ. የዘመዶቻቸው ግፊት መ. ልጅ ስለሌላቸው
2. ከሚከተሉት መካከል የወይዘሮ የአበበች ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ደግነት ለ. ሩህሩህነት ሐ. ጨካኝነት መ. አዛኝነት
3. ወይዘሮ አበበች የህፃናትን ምግብና አልባሳት ለማሟላት ምን ያደርጉ ነበር?
   ሀ. የወርቅ ጌጣጌጣቸውን ሸጠዋል። ሐ. ዳቦ እየጋገሩ ይሸጡ ነበር።
   ለ. ቆሎ እየቆሉ ይሸጡ ነበር። መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።
4. የወይዘሮ አበበች ድርጅት መጠሪያ ስሙ ምን ይባላል?
   ሀ. አበበች ጎበና የህፃናት እንክብካቤና ልማት ማህበር
   ለ. የአበበች ጎበና በጎ አድራጎት ማህበር
   ሐ. የበጎ አድራጎት ድርጅት
   መ. አበበች ጎበና የሃብታሞች ድርጅት
5. ጅማ ዩኒቨርሲቲ ለወይዘሮ አበበች ጎበና የክብር ዶክትሬት ዲግሪ የሰጣቸው በምን ምክንያት ነው?
   ሀ. ዩኒቨርሲቲውን በስራ ስለሚደግፉት
   ለ. ለአገርና ለወገን ባበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ
   ሐ. ዩኒቨርሲቲውን በገንዘብ ስለሚደግፉት
   መ. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ገብተው ስላስተማሩ

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት "የመረዳዳት ጥግ " በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተራ በተራ ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ አንብቡ።

---

## ቃላት

ሀ.በምንባቡ መሰረት በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አቅጣጫ | ሀ. ገዝተው |
| 2. ሸምተው | ለ. ጊዜ |
| 3. ወቅት | ሐ. የቀየረው |
| 4. የላቀ | መ. መስመር |
| 5. የለወጠው | ሠ. ከፍ ያለ |

---

## ጽሕፈት

ሀ."የመረዳዳት ጥግ" ከሚለው ምንባብ ውስጥ ያገኛችሁትን ሃሳብ በአራት ዓፍተ ነገሮች ጻፉ።

ለ. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የሚገኘው የበጎ አድራጎት ክበብ የሚያከናውነውን ተግባር በተመለከተ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

---

## ሰዋስው

ሀ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን የመነሻ ቅጥያዎች ለይታችሁ ፃፉ።

ምሳሌ:- እንደመጣ እንደ-

1. ስለተከለ
2. አስቀረ
3. እየፈጠረ
4. በፍጥነት
5. ከሰጠ
6. እንደ ዕጽዋት
7. ስለቤተሰብ
8. አስመለሰ

ለ.በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን የመድረሻ ቅጥያዎች ለይታችሁ ፃፉ።

ምሳሌ:- ልጁ -ኡ

1. ተማሪዎች
2. ልብስህ
3. በሬዎች
4. መምህሮች
5. መጽሀፌ
6. ክፍላችን
7. ድመቶች
8. እርሳስሽ
9. ቤቱ
10. ስራችሁ

---

ሐ.የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በምሳሌው መሰረት በመነጣጠል ጻፉ።

| | ባለቅጥያ ቃላት | የመነሻ ቅጥያ | ዋና ቃል | የመድረሻ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለልብሶች | ስለ- | ልብስ | -ኦች |
| 2 | ከተወች | | | |
| 3 | በደብተሩ | | | |
| 4 | የአገራችን | | | |
| 5 | እንደሰጠን | | | |
| 6 | አልመሰለም | | | |

---

መ. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በመጠቀም ነጠላ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ።

ምሳሌ:- የባህላችን

- ምግባችን <u>የባህላችን</u> መገለጫ ነው።

1. በወንዞቻችን
2. እንደመምህራችን
3. ስለተጫወትሽ
4. የአገሬ
5. ከመጽሀፍህ

---

**ሠ.በሚከተለው አንቀጽ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ለዩ፤ በመቀጠል የለያችኋቸውን አያያዥ ቃላት በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

ሜላት በትምህርቷ ጥሩ ውጤት ታስመዘግባለች፤ ምክንያቱም ከመምህሮቿ የሚሰጣትን ገለጻ በሚገባ ትከታተላለች የክፍል እና የቤት ስራዋን በመስራት ታጠናለች፡፡ በባህሪዋም የተመሰከረላት ጨዋ ተማሪ ናት፤ ስለሆነም በሰዎች ዘንድ የተወደደች ናት፡፡ መምህሮቿ “ጥሩ ስነ-ምግባር ያስከብራል፤ ነገር ግን የባህሪ ችግር ያለበት ተማሪ በሰዎች ዘንድ አይወደድም፡፡” የሚሏትን ምክር ለጓደኞቿ ትነግራቸዋለች፤ ስለዚህ ሁላችንም በስነ-ምግባር መታነፅ አለብን፡፡

---

## የምዕራፍ ሶስት የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡ በመቀጠልም በፍቻቸው ነጠላ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡

1. ሰበሰበ
2. ራቀ
3. ፍቅር

2. ቅጥያ ማለት ምን ማለት ነው?

3. የመነሻ ቅጥያ ማለት ምን ማለት ነው?

4. የመድረሻ ቅጥያ ማለት ምን ማለት ነው?

5. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በመነጣጠል ጻፉ፡፡

| | ባለቅጥያ ቃላት | የመነሻ ቅጥያ | ዋና ቃል | የመድረሻ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለህዝባችን | | | |
| 2 | እንደችሎታሽ | | | |
| 3 | በመጽሀፉ | | | |
| 4 | ከቀረሽ | | | |

6. አያያዥ ቃትን በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ

7. በቤታችሁ ውስጥ ቤተሰቦቻችሁን በስራ በማገዝ ያከናወናችሁትን ተግባራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

አማርኛ
፬ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አራት
## ስርዓተ-ጾታ

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ርዕሱን በመመልከትና በማዳመጥ ሃሳባችሁን ታካፍላላችሁ፤
- ካነበባችሁት ጽሁፍ ውስጥ ዝርዝር መረጃውን ትጽፋላችሁ፤
- ስለአንቀጽ ምንነት ታብራራላችሁ፤
- የውስት ቃላትን ጥቅም ትዘረዝራላችሁ፤
- ግስ ተጠቅማችሁ አረፍተነገር ትመሰርታላችሁ፤

## ማዳመጥ

### የስራ ክፍፍል



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. የስራ ክፍፍል ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
ለ. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ግለጹ?
ሐ. በቤታችሁ በአብዛኛው የቤት ውስጥ ስራ የሚሰራው ማን ነው? ለምን?

ሀ."የስራ ክፍፍል" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. የእህትየዋ የትምህርት ውጤት ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ የመጣው ለምንድን ነው?
2. እህትየዋ በክበቡ ስለምትሳተፍ በርካታ ቁም ነገሮችን ተምራለች ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. እህትየዋ የተቆጨችው በምን ምክንያት ነው?
4. አባትየው የስራ ክፍፍልን በተመለከተ ምን ዓይነት አመለካከት ያላቸው ይመስሏችኋል?

## ቃላት

ሀ.“የስራ ክፍፍል” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በ “ሀ” ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ “ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. አካባቢ | ሀ. ማወቅ |
| 2. መማር | ለ. መጸጸት |
| 3. ተረዷት | ሐ. አመለካከት |
| 4. መቆጨት | መ. ሠፈር |
| 5. አስተሳሰብ | ሠ. መተባበር |
| | ረ. ተገነዘቧት |

ለ.ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

1. የበለጠ
2. በቅርብ
3. ለቀቀ
4. ርህራሔ
5. በቡድን

---

## ጽሕፈት

ሀ. ከዚህ በታች በተሰጧችሁ ቃላት ዓረፍተነገሮች መስርቱ፡፡

1. መቀነስ
2. ክበብ
3. አባላት
4. ሥራ
5. ጫና

ለ. በቤታችሁ በጾታ እኩልነት ላይ የተመሰረተ የስራ ክፍፍልን የሚያሳይ ጽሁፍ በአራት ዓረፍተ ነገሮች በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

---

## ቃላት

ሀ. አማርኛ ቋንቋ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ቋንቋዎች በመዋስ እየተጠቀመባቸው ያሉ ቃላትን ከመጽሀፍት እና ሰዎችን በመጠየቅ ከሰበሰባችሁ በኋላ ማስታወሻ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡


---

ሀ. በየሳጥኑ መሃል ላሉ ቃላት ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ተመሳሳይ የሚሆኑትን አራት ቃላት በመምረጥ በእያንዳንዱ ሳጥን ዙሪያ አሟሉ፡፡


የተሰጡ አማራጭ ተመሳሳይ ቃላት

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፌሽታ | መድከም | ከመረ | በተነ | ፈጸመ | አስተላለፈ | ቆለለ | መኳተን | ፈንጠዝያ | አዳረሰ |
| አከናወነ | አጠራቀመ | አስፋፋ | ሃሴት | መልፋት | አጠናቀቀ | ፍስሃ | አከማቸ | መትጋት | አዘጋጀ |


ምሳሌ፡-





1.





2.




3.




4.



## ንባብ

### የፆታ እኩልነት



## ቅድመ ንባብ

ሀ. የፆታ እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?
ለ. ስዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን የሚያወራ ይመስላችኋል?
ሐ. በቤታችሁ ዉስጥ ምን ምን አይነት ስራ ትሰራላችሁ?
መ. በስራቸው ታዋቂ የሆኑ ሴቶችን ታውቃላችሁ? ምን ምን ተግባራትን ፈፅመው የታወቁ ናቸው?

የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑ አባት፣ እናት እና ሁለት ልጆች በጠዋት ተነስተው ወደ ስራ እና ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ዝግጅት እያደረጉ ሳለ እናት ወይዘሮ ኤልሳ
*መጣራት ጀመሩ፡-*

ወይዘሮ ኤልሳ፡- ሰላም ! . . . ሰላም ! . . . ኧረ ሰላም!

ሰላም፡- አቤት እማዬ ምን ሆነሽ ነው?

ወይዘሮ ኤልሳ፡- እኔ ወተቱን እያፈላሁ እና እንዳይገነፍልብኝ እየጠበኩ ስለሆነ አንቺ የተጣደውን ድስት እንድታማስይልኝ ነው፡፡

ሰላም፡- እማዬ.... የደንብ ልብሴን አለበስኩም ፤ ደብተሬንም አላዘጋጀሁም፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- ወንድምሽን ጥሪውና ንገሪው ፣ ደብተርሽን አስተካክሎ በቦርሳሽ ውስጥ ያስገባልሽ፡፡

ሰላም፡- እንዴ! እማዬ ኤርሚያስ እንዴት አድርጎ የኔን ደብተር ያስተካክልልኛል? ሁሉንም ደብተሮች እኮ ይዤ አልሄድም፤ በክፍለ ጊዜ መሰረት ዛሬ ምን እንደምንማር እሱ አያውቅም፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- ያም ሆነ ይህ ያዘዝኩሽን ስራ ስሪ፤ ለማዘጋጀቱ እንደሆነ ትደርሺበታለሽ፡

አቶ ነብዩ፡- በጠዋት ተነስታችሁ ብትዘገጃጁ ጥሩ ነበር፡፡ ይሄው እኛ ተነስተን ከተቀመጥን እንኳን ስንት ጊዜያችን፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- ወይ ጉድ አንተና ኤርሚያስ ምን ስራ ትሰራላችሁ፣ በጠዋት ተነስታችሁ የግል ንፅህናችሁን ከጠበቃችሁ በኋላ ልብሳችሁን ለብሳችሁ፣ ቁርስ መብላት ነው፡፡

ሀ. በቤተሰቡ ውስጥ ስራ እየሰሩ ያሉት እነማን ናቸው?
ለ. ከዚህ በኋላ ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?

ኤርሚያስ፡- እማዬ እኔ እኮ እንደ ሰላም ስራ ላግዝሽ እችል ነበር፤ አባዬና አንቺ ግን ይሄ የሴት ስራ ነው፤ አንተ ማዕድቤት ለማዕድቤት ምን ያስኬድሃል እያላችሁ ትገስጹኛላችሁ፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- አዎ ልጄ ጥፋቱ የኔና የአባትህ ነው፡፡ አባትህ በፆታ እኩልነት ለማመን ይቸገራል፡፡ እኔም ብሆን የተለያዩ ሁኔታዎችን ከጎረቤትም ሆነ

ከመገናኛ ብዙሃን ባዳምጥም አስተዳደጌ ከፍተኛ ተፅእኖ አሳድሮብኛል፡፡

አቶ ነብዩ፡- እኔ የውጭውን ስራ ስሰራ እውላለሁ፤ አንቺ ደግሞ በቤት ውስጥ ያለውን ስራ ሰርተሽ ብትጠብቂኝ ምን ችግር አለው?... ሌላው ኤርሚያስ ከትምህርትቤት እንደተመለስክ የጥናት ሰዓትህን ጠብቀህ እንድታጠና፡፡

ኤርሚያስ፡- አባዬ! . . . ሁልጊዜ እኔን ብቻ አጥና የምትለኝ ለምንድን ነው? ሰላምም ማጥናት አለባት፡፡

ሰላም፡- አዎ እኔን አንድም ቀን አጥኚ ብለኸኝ አታውቅም፡፡

አቶ ነብዩ፡- ልጆቼ የተናገራችሁት ነገር ውስጤን በጣም አስደንግጦታል፡፡ ሁለታችሁንም የምንወዳችሁ ልጆቻችን ናችሁ፡፡ ሰላም የማዕድቤት ስራ እንድትሰራ አንተ ደግሞ እንድታጠና አድልቼ አይደለም፡፡ እናታችሁ ከአንተ ይልቅ ሰላም ስራ እንድታግዛት ስለምትፈልግ ነው፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- እኔ ሰላም እንድታግዘኝ ስለምፈልግ አይደለም፤ ሁልጊዜ የምጠራት ፤ በለመድኩትና ባደኩበት ልማድ ውስጥ ስላለሁ ብቻ ነው እንጂ እኔም ሆንኩ ሰላም የማዕድቤት ስራ ብቻ እንድንሰራ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች የሉም፡፡ ሁላችንም ተጋግዘን መስራት ይገባናል፡፡ ሰላምም እንደ ወንድሟ ትምህርቷን በሚገባ እንድትከታተል እድል ልንሰጣት ይገባል፡፡

ኤርሚያስ፡- ከዚህ በፊት ያለፈው አልፏል፤ ለወደፊቱ ምን እናድርግ? በሚለው ብንወያይ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

ሰላም፡- አዎ ከዚህ በኋላ አባዬ እና ወንድሜ ወጥ መስራት፣ ቡና ማፍላት፣ ግቢ ማፅዳት፣ አልጋ ማንጠፍና ቤት ማዘጋጀት መልመድ መቻል አለባችሁ፡ እኔ ወንድሜን አለማምደዋለሁ፤ እማዬ ደግሞ አባዬን አለማምጂው፡፡ ከዚህ በኋላ ዕቅድ አውጥተን ስራችንን እንስራ፡፡

ቤተሰቡ በሙሉ በሰላም ሃሳብ በመስማማት በቤት ውስጥ የስራ ክፍፍል ዕቅድ በማውጣት እና በዕቅዳቸውን መሰረት በመስራት በቤታቸው ውጤታማ የሆነ የስርዓተ-ጾታ አመለካከት እንዲኖር ማድረግ ቻሉ፡፡

---

ሀ.“የጾታ እኩልነት “ በሚል ርዕስ በቀረበው ጭውውት መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች  በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ወይዘሮ ኤልሳ ሰላምን የጠሯት ለምንድን ነው?
2. የእነ አቶ ነብዩ ቤተሰብ ከአጉል ልማድ እንዴት መላቀቅ ቻለ?
3. የሰላም ቤተሰቦች በሰላም ላይ ያሳደሩት አሉታዊ ተፅዕኖ ምን ነበር?
4. ቤተሰቡ እየተወያየ የነበረው በየትኛው ጊዜ ነው?
5. ጎረቤቶቻቸው ስለ ስርዓተ-ጾታ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

---

## ጽሕፈት

ሀ.”የጾታ እኩልነት” በሚል ርዕስ በቀረበው ጭውውት መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ስራን ተከፋፍሎ መስራት ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
2. ስርዓተ-ጾታ ማለት ምን ማለት ነው?
3. የጭውውቱ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

---

## ቃላት

ሀ.“የጾታ እኩልነት “ በሚል ርዕስ በቀረበው ጭውውት መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ጻፉ ፡፡

ምሳሌ፡-   ገነፈለ = ፈሰሰ

1. መርሀ-ግብር
2. መገሰጽ
3. መቸገር
4. ተጽዕኖ
5. መወያየት
6. አመለካከት
7. ማገዝ
8. ማለማመድ

---

## መናገር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ እና የመከራከሪያ ርዕስ መሰረት አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብ እንዲሁም ዳኛ በመምረጥ ክርክር አቅርቡ፡፡

### የክርክር ርዕስ

በቤት ውስጥ የወንዶች እና የሴቶች ሚና ምን መሆን አለበት?

---

## ጽሕፈት

ሀ.የሚከተሉትን የተዘበራረቁ ዓረፍተነገሮች ቅደም ተከተል በማስተካከል አንቀጽ ጻፉ፡፡

1. የታሸው ዳማከሴ ትንሽ እንዲቆይ አደረጉ፡፡
2. ዮሴፍ ቆሻሻ ሸተተው፡፡
3. ዳማከሴ ቆርጠው በመዳፋቸው አሹ፡፡
4. እናቱ በጣም ተጨነቁ፡፡
5. እራሱን አመመው፡፡
6 የእራስ ምታቱም ቀነሰለት፡፡
7. በግማሽ ማንኪያ አድርገው አጠጡት፡፡

ለ.የሚከተለውን የቀለሞች ፍንጭ እንደአቀማመጣቸው በመከተል ከታች ባለው ሳጥን ውስጥ ያሉትን ቃላት በቅደም ተከተላቸው በማገጣጠም አንቀጽ ጻፉ፡፡

የቀለሞች ፍንጭ፡-

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ | 6ኛ | 7ኛ |

መነሻ ቀለም፡- ቢጫ

ማጠናቀቂያ ቀለም፡- ብቱካናማ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማንሳት ይቻላል፡፡ | አባባል | የሚለውን | ናት፡፡” | ልጅ |
| ሴቶች | የማገናዘብ | ችሎታቸውም | ብልህ | “ሴት |
| አላቸው፡፡ | ለአገር | ዘንድ | ከፍተኛ | ለዚህም |
| ጥበብም | በማህበረሰቡ | ባለውለታዎች | ይታወቃል፡፡ | ነው፡፡ |
| ብልሃትና | ጥንካሬያቸውም | አስተሳሰባቸውም | ናቸው፡፡ | ከችኩልነት |
| ነው፡፡ | ብሩህ | ይመርጣሉ፡፡ | መረጋጋት | ይልቅ |

---

## ሰዋስው

### ሀ.በምሳሌው መሰረት በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- እስማኤል አንደኛ ስለወጣ ተደሰተ፡፡ ተደሰተ

1. በርናባስ ወደትምህርት ቤት ሄደ፡፡
2. ናሆም በጥሩ ስነ-ምግባር ታነፀ፡፡
3. የትምህርት ቤታችን ርዕሰመምህር ለተማሪዎች ምክር ሰጡ፡፡
4. ሂክማ ባሳየችው ጥሩ ባህሪ ተሸለመች፡፡
5. በአገራችን ለባህላዊ ሕክምና የሚያገለግሉ በርካታ እጽዋቶች ይገኛሉ፡፡
6. የገዳ ስርዓት አንዱ የዲሞክራሲ መገለጫ ነው፡፡
7. ኢትዮጵያ በርካታ ቅርሶችን በዮኔስኮ አስመዝግባለች፡፡
8. የተጣሉ ሰዎችን ለማስታረቅ ሽምግልና ተቀመጡ፡፡
9. ሴቶች በከፍተኛ የአመራርነት ደረጃ ላይ አገለገሉ፡፡
10. የህዳሴው ግድብ ኃይል ማመንጨት ጀመረ፡፡

---

### ለ.በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ስም የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ፡፡

1. ትልቅ ዳቦ በላሁ፡፡
2. መፅሃፍ ተገዛልኝ፡፡
3. አልማዝ ጎበዝ ናት፡፡
4. ጥቁር ጫማ አለኝ፡፡
5. አዲስ አበባ ታምራለች፡፡

---

ሐ.በሚከተለው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙትን ግሶች ብቻ በመለየት ጻፉ።



ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ የተጣለው መጋቢት 24/ 2003 ዓ.ም ነው። ግድቡ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ልዩ ስሙ ጉባ በተባለ ወረዳ ይገኛል። ግድቡ በኢትዮጵያዊያን ዕውቀት፣ ገንዘብ እና ጉልበት የሚሰራ ሲሆን ሲጠናቀቅም 6,450 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ያመነጫል። ይህም ኃይል የኢትዮጵያዊያንን ሁለንተናዊ ችግሮች ይፈታል። በመሆኑም ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ትልቅ ኩራትና የጀግንነታችን መገለጫ የሆነ የዚህ ትውልድ አሻራ ነው። በመሆኑም ግድቡን ለማጠናቀቅ እኛ ኢትዮጵያዊያን በአንድነት ልንረባረብ ይገባል።

መ.በምሳሌ መሰረት የተሰጧችሁን ግሶች ወደ ስም ቀይራችሁ ፃፉ።

| ተ.ቁ | ግስ | ስም |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ገነባ | ግንብ |
| 1 | ዘፈነ | |
| 2 | ተማረ | |
| 3 | ቀለደ | |
| 4 | ሰራ | |
| 5 | ጨፈረ | |

ሠ.በሚከተለው ምሳሌ መሰረት በተሰጡት ግሶች ዓረፍተነገሮች መስርቱ።

ምሳሌ፡- ሰራ - ምንተስኖት የቤት ስራውን በወቅቱ ሰራ።

1. መነዘረ
2. ተናገረ
3. መጣ
4. ጨመረ
5. ገመገመ
6. ወደደ

## የምዕራፍ አራት የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው አጭር መልስ ስጡ፡፡
   ሀ. የውሰት ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ
   ለ. ስም ማለት ምን ማለት ነው?
   ሐ. አከናወነ፣ አለ፣ ናቸው፣ ተሰበረ በሚሉ ግሶች ዓረፍተ ነገር መስርቱ?
   መ. የዕለት ውሎአችሁን በተመለከተ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

2. የሚከተሉት ቃላት ስም ወይም ግስ መሆናቸውን ለዩ፡፡

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጠየቀ | ቡና | መዘዘ | አፈላች | በር | በሳ | ዕውቀት | |
| ትምህርትቤት | ማረከ | ሰላም | መብራት | ጠቀለለ | አጥር | ደባለቀ | |

3. የሚከተሉትን ግሶች ወደ ስም ቀይራችሁ ጻፉ፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አመነ | ገነባ | ሳለ | ተደሰተ | ለመነ | አደገ | ቻለ |

አማርኛ
፬ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አምስት
## ጉብኝት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ስለጉብኝት መዳረሻዎች ያዳመጣችሁትን በቃላችሁ ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡
- ምንባብ አንብባችሁ የተረዳችሁትን ትገልጻላችሁ፡፡
- የአንቀጽ ባህሪያትን ትለያላችሁ፡፡
- አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡
- ገላጮችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

## ማዳመጥ



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?
ለ. ፎቶግራፉን ስትመለከቱ ምን ተረዳችሁ?
ሐ. ለታሪካዊ ቅርሶች ምን አይነት ጥበቃ መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?

### ሀ."የሼህ ሆጀሌ ቤተ-መንግስት" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. የሼህ ሆጀሌ ቤተ-መንግስት ከተሰራ ስንት አመታትን አስቆጥሯል?
2. የሼህ ሆጀሌ ቤተ-መንግስት የሚገኘው በየትኛው ክፍለ ከተማ ነው?
3. የሼህ ሆጀሌን ህንፃ ለመስራት ጥቅም ላይ የዋሉ ዋና ዋና ቁሳቁሶች ምን ምን ናችው?
4. ለአቶ አብዱራህማን ሼህ ሆጀሌ ምኑ ናቸው?
5. ቅርሶችን ጠብቆ ለማቆየት ምን መደረግ አለበት?

### ቃላት

ሀ. "የሼህ ሆጀሌ ቤተ-መንግስት" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉት ቃላት የያዙትን አውዳዊ ፍቺ በቃላችሁ አብራሩ፡፡

1. በወቅቱ
2. ቱሪስት
3. ቅርስ
4. ማዕከል
5. ጥቅም
6. ወለል

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

1. በርካታ
2. ሰፊ
3. ከስር
4. የተለየ
5. ወርደው
6. ጨለማ

---

ሐ.በምሳሌው መሰረት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት የያዙት ሃሳብ ትርጉም የሚሰጠው በማጥበቅ ወይንም በማላላት ሲነበብ መሆኑን ለዩ፡፡

ምሳሌ፡- አለኝ

የአማርኛ መጽሐፍ አለኝ፡፡ ጠብቆ

እመጣለሁ አለኝ፡፡ ላልቶ

1. በዓለም ላይ ረጅሙ ወንዝ የኢትዮጵያው አባይ ነው፡፡

 የሰው ልጅ በባህሪው አባይ መሆን የለበትም፡፡

2. በተናገረኝ መጥፎ ነገር ሳር ከምውል መከርኩት፡፡

 የመናፈሻ ቦታው ሳር ለብሷል፡፡

3. ለሰዎች ሁሉ አዛኝ መሆን ያስፈልጋል፡፡

 እናቴ አዛኝ ያልሰራሁት ስራ የለም፡፡

4. የሌብነት ተግባር የሚፈጽም ሰው ሽፍታ ነው፡፡

 ፊቱ ላይ ሽፍታ ወጣበት፡፡

5. ከስፖርት ዓይነቶች ውስጥ አንዱ ውሃ ዋና ነው፡፡

 ማስረሻ የትምህርት ቤታችን ዋና ርዕሰ መምህርት ናት፡፡

6. አዲስ አበባ ውስጥ ሰባ ደረጃ የሚባል ቦታ አለ፡፡

 በሬው በሚገባ ስለተቀለበ ሰባ፡፡

## ጽሕፈት

### ሀ.በምሳሌው መሰረት የሚከተሉት ቃላት በማጥበቅ እና በማላላት ስናነባቸው የሚሰጡትን የተለያየ ትርጉም የሚያሳይ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

1. ሰውየው ራሱ በራ ነው፡፡ ("በራ" የሚለው ቃል በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ የምናነበው በማላላት ነው፡፡) በዚህ ዓረፍተ ነገር መሰረት ትርጉሙ እራስ ፀጉሩ ወደኋላ የሸሸ የሚል ይሆናል፡፡

2. የሳሎኑ መብራት በራ፡፡ ("በራ" የሚለው ቃል በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ የምናነበው በማጥበቅ ነው፡፡) በዚህ ዓረፍተ ነገር መሰረት ትርጉሙ ብርሃን ሰጠ የሚል ይሆናል፡፡

1. ቀናት
2. አያት
3. ለጋ
4. ያነባል
5. ጥልቅ

### ለ.ከዚህ በታች በተሰጧችሁ ቃላት ዓረፍተነገሮች መስርቱ፡፡

1. ታነጸ
2. አጌጠ
3. ስልጣኔ
4. የተለየ
5. ታሪካዊ
6. ተሳታፊ
7. ድንቅ
8. ውበት

### ሐ."የሼህ ሆጀሌ ቤተ-መንግስት" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን የምንባብ ሃሳብ በአራት ዓረፍተነገሮች ጻፉ፡፡

## ንባብ

### አዲስ አበባ እና ቤተ-መዘክሮቿ (ሙዚየሞቿ)



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም



የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሙዚየም



የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም



የፖስታ ሙዚየም

## ቅድመ ንባብ

ሀ. ቤተ-መዘክር ወይም ሙዚየም ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?
ለ. ፎቶዎቹን በማየት ምንባቡ ምን ሊነግራችሁ እንደሚችል ገምቱ?
ሐ. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የምታውቋቸውን የጉብኝት ስፍራዎች ዘርዝሩ?

በአዲስ አበባ ከተማ የኢትዮጵያ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ተሰባስበው የሚገኙባቸው ውስጥ ሙዚየሞች አሉ፡፡

ከእነዚህም ውስጥ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሙዚየም፣ የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም፣ የኢትዮጵያ ፖስታ ሙዚየም፣ አዲስ አበባ ሙዚየም፣ የርዕሰ አድባራት እንጦጦ ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ሙዚየም፣ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ሙዚየም፣ የመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሙዚየም፣ የቀይ ሽብር ሰማዕታት ሙዚየም፣ የታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ቤተክርስትያን ሙዚየም፣ የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ሙዚየም፣ የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሙዚየም፣ መንበረ ፓትርያርክ ቤተ-መጽሐፍት ሙዚየም፣ የስፖርት ሙዚየም ጃንሜዳ፣ የነገሥታት ባቡሮች ሙዚየም - ለገሃር ባቡር ጣቢያ ወ.ዘ.ተ ይገኙበታል፡፡ ከእነዚህ አሥራ አምስት ሙዚየሞች ውስጥ አራቱን እናስተዋውቃችሁ፡፡

ሀ. ከላይ ከተጠቀሱት ሙዚየሞች ውስጥ እናንተ የጎበኛችሁት ሙዚየም አለ? የትኛው ነው?
ለ. ከላይ ከተጠቀሱት ሙዚየሞች ምንባቡ የትኞቹን ሊያስተዋውቃችሁ እንደሚችል ገምቱ?

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ነው፡፡ ይህም በ1936ዓ.ም መጨረሻ የተመሠረተ ሲሆን በውስጡ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ እነዚህም ክፍሎች የቅርስ ጥበቃ፣ የመረጃ እንዲሁም የአውደ ርዕይ ክፍሎች ይባላሉ፡፡ በሙዚየሙ ውስጥ የአርኪዮሎጂ፣ የጥንታዊና የመካከለኛ ዘመን ቅርሶች፣ የሰዎች ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች እንዲሁም የተለያዩ ብሔረሰቦች ባህላዊ ቁሳቁሶች ይገንኙበታል፡፡

የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሙዚየም ሌላው ነው፡፡ ይህ ሙዚየም በፊት ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት በሚባለውና የአጼ ኃይለሥላሴ ቤተ-መንግሥት በነበረው፤ አሁን ደግሞ 6ኪሎ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተብሎ በሚታወቀው ግቢ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ይህኛው ደግሞ ስለኢትዮጵያ የተሠሩ የጽሑፍ ሥራዎችንና በኢትዮጵያ ያሉ ብሔረሰቦች ባህልና ታሪክ የሚያሳዩ መረጃዎች የተሰባሰቡበት ነው፡፡ በዚህ ሙዚየም ውስጥ ቤተ-መጻሕፍትም ይገኝበታል፡፡ ሌላው የምናስተዋውቃችሁ አራትኪሎ የሚገኘው የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም ይባላል፡፡ በዚህ ሙዚየም ውስጥ ብዙ ቁጥር ያላቸው የዱር እንስሳት፣ አእዋፋት፣ የውሃ ውስጥ ፍጥረታት ይገኛሉ፡፡ የሚገርማችሁ በዚህ ሙዚየም ውስጥ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ እንስሳትንም ለማየት ትችላላችሁ፡፡ ይህ ሙዚየም በኢትዮጵያ ውስጥ ብቸኛው የዱር እንስሳት፣ የአእዋፍና የውሃ ውስጥ

ፍጥረታት ለእይታ ቀርበው የሚገኙበት ነው:: በሙዚየሙ ከሦስት ሺህ አምስት መቶ በላይ የተለያዩ ዓይነት እንስሳትና ከአንድ ሺህ አንድ መቶ በላይ የእንስሳት ዝርያዎች ይገኛሉ::

የኢትዮጵያ ፖስታ ሙዚየም ሌላውና አራተኛው የምናስተዋውቃችሁ ሙዚየም ነው:: ይህ ሙዚየም በዓለማችን ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ የታተሙና በዓለም ፖስታ አባል አገራት የሚላኩ ቴምብሮች ተሰባስበው ለእይታ የሚቀርቡበት ነው:: ቴምብሮቹ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ ውብ የተፈጥሮ መስህቦችን፣ የብሔረሰቦችን ባህል፣ የታዋቂ ሰዎችን፣ የእጽዋትንና የአእዋፋትን ብሎም የእንስሳትን ምስል የሚያሳዩ ናቸው:: እነዚህ ቴምብሮች በፖስታ ላይ ተለጥፈው በዓለም አገራት ሲዞሩ አገራችንን ያስተዋውቃሉ::

ሙዚየሞችን መጎብኘት የአገር ታሪክ፣ የጀግኖችን ገድልና ሥራ፣ ባህል፣ ቅርስ . . . እንድናውቅ ያደርጋል:: እናንተም ያስተዋወቅናችሁንና የቀሩትን ሙዚየሞች በተገኘው አጋጣሚ ጎብኙ እንላለን::

(ምንጭ:- አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ 78ኛ ዓመት፣ ቁጥር181፣ መጋቢት 1 ቀን 2011ዓ.ም፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ፣ ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተደርጎ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## መናገር

### ሀ.ቀጥሎ የቀረቡት ዓረፍተነገሮች "አዲስ አበባ እና ቤተ-መዘክሮቿ (ሙዚየሞቿ)" በሚለው ምንባብ መሰረት የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ከምንባቡ ማስረጃ በማቅረብ በልቃ አብራሩ::

1. ሙዚየሞች የአንድን አገር ባህልና ታሪክ መገለጫ ቅርሶችን የሚይዙ የጉብኝት ቦታዎች ናቸው::
2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ቀደም ሲል ገነተ ልዑል ቤተ-መንግስት በመባል ይታወቅ ነበር::
3. ብዙ ቁጥር ያላቸው የቤት እንስሳትና አዕዋፋት የሚገኙት በተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም ውስጥ ነው::
4. በፖስታ ላይ የሚለጠፉ ቴምብሮች ፋይዳቸው አገራችንን ለዓለም አገራት ማስተዋወቅ ነው::
5. ሙዚየም መጎብኘት ከመዝናኛነት ያለፈ ጥቅም የለውም::

## ቃላት

ሀ.ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በምንባቡ መሰረት ስጡ።

1. ታሪካዊ
2. ምስል
3. ገድል
4. መለጠፍ
5. ጥበቃ

ለ.ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በምንባቡ መሰረት ስጡ።

1. ውብ
2. መሰረተ
3. ተፈጥሯዊ
4. ቀረበ
5. ፈጠራ

## ጽሕፈት

ሀ.በ"ሀ" ረድፍ ለተደረደሩ የሙዚየም መገለጫዎች ከ"ለ" ረድፍ ከተዘረዘሩ የሙዚየም ዓይነቶች ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 1. የታተሙና በዓለም አገራት የሚላኩ ቴምብሮች ተሰባስበው የሚገኙበት፤ | ሀ. የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ሙዚየም |
| 2. የዱር እንስሳት፣ አዕዋፋትና የውሃ ውስጥ ፍጥረታት የሚገኙበት፤ | ለ. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም |
| 3. ስለኢትዮጵያ የተጻፉ የጽሑፍ ስራዎችና ቤተ-መጽሐፍ የሚገኝበት፤ | ሐ. የኢትዮጵያ ፖስታ ሙዚየም |
| 4. ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት፤ | መ. የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም |

## ለ. በሳጥኑ ውስጥ የተቀመጡትን ቃላት በክፍት ቦታዎች ውስጥ በማስገባት ዓረፍተ ነገሮቹ የተሟላ ሃሳብ እንዲሰጡ አድርጉ፡፡

| ብርቅዬ | ቴምብር | ቤተ-መዘክሮች | ቅርሶች | መጎብኘት |
|---|---|---|---|---|

1. ሙዚየም ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ____________የሚገኙበት ስፍራ ነው፡፡
2. በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ እንስሳት ________________እንስሳት ይባላሉ፡፡
3. __________በፖስታ ላይ የሚለጠፍ አገርን የሚያስተዋውቅ ሕጋዊ ማረጋገጫ ነው፡፡
4. ቤተ-መዘክሮችን ______________አገርን ማወቅ ነው፡፡
5. ቅርሶች በሚገባ ተጠብቀው እንዲቆዩ ____________ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

## ሐ.ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ጻፉ፡፡

1. ቅርስ
2. ብሔራዊ
3. ፍጥረት
4. እይታ
5. መስህብ
6. ባህል
7. ፈጠራ

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ፡፡**



## አዲስ አበባችን

አዲስ አበባ እጅግ ውብ እና ፅዱ እየሆነች ያለች ከተማ ናት፡፡ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በየመንገዱ ግራና ቀኝ የተተከሉ እጽዋቶች እና የፈኩ አበባዎች፤ እየተገነቡ ያሉ ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች፤ ልዩ የሆነ ውበት አጎናፅፈዋታል፡፡ በከተማዋ ውስጥ የተሰሩ እንደ እንጦጦ እና አንድነትን የመሳሰሉ የጉብኝት ፓርኮች እግር ጥሎት ለተመለከታቸው ልብን በሃሴት እንዲሞላ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህንና መሰል ልዩ ልዩ መዝናኛዎችን በውስጧ አቅፋ ስለያዘች በየቀኑ የሚጎበኛትን አያሌ ሕዝብ “አዲስ አበባ ውቧ ከተማዬ!” የሚል ስሜት እንዲሰማው ያደርጋሉ፡፡ በከተማዋ ዙሪያ በሚገኙ ተራራዎች ላይ ሆኖ በምሽት ቁልቁል ለሚመለከታትም በከዋክብት ያሸበረቀች ሰማይ መስላ በብርሃን ደምቃ ትታያለች፡፡

## ጽሕፈት

ምሳሌ፡- 1. የደንብ ልብሱን ቀየረ፡፡

2. ምንተስኖት 10፡00 ሲሆን ከትምህርት ቤት ተመለሰ፡፡

3. በመጨረሻም ከእህቱ ጋር በመሆን የግቢያቸውን አትክልት ውሃ አጠጣ፡፡

4. የተሰጡትን የቤት ስራዎች ሰርቶ ጥናቱን አጠና፡፡

5. ጥቂት ረፍት አደረገ፡፡

ምንተስኖት 10፡00 ሲሆን ከትምህር ትቤት ወደቤት ተመለሰ፡፡ ቤት እንደደረሰም የደንብ ልብሱን ቀይሮ ጥቂት ረፍት ካደረገ በኋላ የተሰጡትን የቤት ስራዎች ሰርቶ ጥናቱን አጠና፡፡ በመጨረሻም ከእህቱ ጋር በመሆን የግቢያቸውን አትክልት ውሃ አጠጣ፡፡

ሀ.ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተል በማስተካከል አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

1. ጓደኛዋ ቀስበቀስ የምልክት ቋንቋውን አለማመደቻት፡፡

2. የምልክት ቋንቋ የምትችለው ጓደኛዋ እንድታለማምዳት ጠየቀቻት፡፡

3. በዚህም ደስተኛ ሆነች፡፡

4. ዓይናለም የምልክት ቋንቋ ለመልመድ ትፈልጋለች፡፡

5. ዓይናለም በአጭር ጊዜ የምልክት ቋንቋ መጠቀም ቻለች፡፡

---

ለ.ዛሬ ጠዋት ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከገባችሁበት ሰዓት አንስቶ እስከ እረፍት ሰዓት ድረስ የሰራችሁትን ዋና ዋና ተግባራት የአንቀጽ ባህርያትን በመጠበቅ በአንድ አንቀፅ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

---

## ሰዋስው

### ሀ.በዝርዝር ለተቀመጡ ገላጭ ቃላት ምላሽ የሚሆኑ የገላጭ ቃላት ዓይነቶችን ከሳጥኑ ውስጥ በመምረጥ ጻፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| መጠን | ቀለም | ወገነ |
| ብዛት | ባህሪ | ቅርጽ |

1. አረንጓዴ፣ጥቁር፣ሰማያዊ፣ነጭ . . .
2. አያሌ፣ሺህ፣ብዙ፣አንድ . . .
3. ክፉ፣ደግ፣የዋህ፣ጥሩ . . .
4. ኢትዮጵያዊ፣ኤርትራዊ፣ኬንያዊ ፣. . .
5. ክብ፣ሞላላ፣ጥምዝ፣ሾጣጣ . . .
6. አጭር፣ወፍራም፣ቀጭን፣ረጅም. . .

---

### ለ.በምሳሌው መሰረት በክፍት ቦታው ላይ ተገቢውን ገላጭ ቃል በማስገባት ዓረፍተነገሩን አሟሉ፡፡

ምሳሌ፡- ታታሪ ሰው እወዳለሁ፡፡

1. ________መጽሐፍ ተቀደደ፡፡
2. አባቴ ______________ቦርሳ ገዛልኝ፡፡
3. ወንድሜ____________ቤት ሰራ፡፡
4. ዛፉ________________ነው፡፡
5. ትምህርትቤታችን____ ነው፡፡

---

### ሐ.በምሳሌው መሰረት በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ገላጭ ቃላት በመለየት ጻፉ፡፡


ምሳሌ፡- ዓለማችን ሞላላ ቅርጽ አላት፡፡ ሞላላ

1. ቸር ሰው ያለውን ያካፍላል፡፡
2. በርካታ ህዝብ በተገኘበት የፍቼ ጫምባላላ በዓል ተከበረ፡፡
3. ኢትዮጵያዊ አለባበሳችን ያምራል፡፡
4. ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ትልቅ ግድብ ገነባች፡፡
5. ነጭ በትር የዓይነ-ስውር መሪ ነው፡፡

---

**መ.የሚከተሉትን ገላጭ ቃላት በየምድባቸው ስር አስቀምጡ፡፡**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያዊ | ግራጫ | በርካታ | ክብ | ቢጫ | ዝርግ |
| ጥቂት | ሩህሩህ | ሰፊ | የዋህ | አነስተኛ | ሱዳናዊ |
| ሶስትመዓዘን | ኤርትራዊ | ጥቁር | ጠባብ | ቀጭን | አዛኝ |
| ወይንጠጅ | ቸር | ትልቅ | ኬኒያዊ | ጠፍጣፋ | ብዙ |




**ሠ.በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ገላጭ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፡- አያሌ - በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አያሌ ህዝብ ተሳተፈ፡፡

1. ቀይ
2. መጥፎ
3. ቻይናዊ
4. አጭር
5. ሩህሩህ

## የምዕራፍ አምስት የክለሳ ጥያቄዎች

1. የአንቀጽ ባህርያትን በዝርዝር አስረዱ?
2. ገላጭ ቃል ማለት ምን ማለት ነው?
3. የሚከተሉትን ገላጭ ቃላት ዓይነታቸውን ግለፁ፡፡ በመቀጠል ዓረፍተነገር መስርቱባቸው፡፡
   - ድንክ
   - ድቡልቡል
   - አዛኝ
   - ወርቃማ
   - ጥቂት
4. በአዲስ አበባ ከተማ ከጎበኛችሁት ስፍራ ውስጥ ወይም የጎበኙ ሰዎችን በመጠየቅ እጅግ ስለማረካችሁ ጉዳይ የአንቀጽ ባህርያትን ያሟላ አንድ አንቀጽ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት
## ስፖርት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ታዳምጡና በቃል ሃሳባችሁን ትለዋወጣላችሁ።
- እያንዳንዱን አንቀጽ አንብባችሁ ከጽሁፉ ውስጥ ያገኛችሁትን ሃሳብ ታብራራላችሁ።
- የቃላት እውቀታችሁን ታሳድጋላችሁ።
- ባለቤትና ግስን አስማምታችሁ አረፍተነገር ታዋቅራላችሁ።

## ማዳመጥ

### የኦሎምፒክ ፈርጦች




## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ለ. የምትመለከቷቸው ፎቶግራፎች የነማን ናቸው? ለአገራቸው ምን እንዳበረከቱስ ታውቃላችሁ? የምታውቋቸውን የስፖርት ዓይነቶች ተናገሩ?

ሀ.“የኦሎምፒክ ፈርጦች” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. በተከታታይ የሮም እና የቶኪዮ የኦሎምፒክ ማራቶን ውድድሮችን ያሸነፈው አትሌት ማን ይባላል?
2. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በስሟ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሰየመላት አትሌት ማን ትባላለች?
3. “ኢትዮጵያ የሌለችበት ኦሎምፒክ አይደምቅም!” የተባለው ለምንድን ነው?
4. ኃይሌ ገብረስላሴ ተደጋጋሚ ድሎችን እንዲያስመዘግብ የገፋፋው ምንድን ነው?

---

ለ.“የኦሎምፒክ ፈርጦች” በሚለው ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. በ 10ሺህ ሜትር የኦሎምፒክ ውድድር የመጀመሪያዋ ጥቁር አፍሪካዊት የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ አትሌት ማን ናት?

   ሀ. ጥሩነሽ ዲባባ ለ. ደራርቱ ቱሉ ሐ. መሰረት ደፋር መ. ቀነኒሳ በቀለ

2. ብራዚል በዓለም ዋንጫ ተሳትፎ ስትታወቅ ኢትዮጵያ ደግሞ በ________ተሳትፎ ትታወቃለች፡፡

   ሀ. በኦሎምፒክ ለ. በአፍሪካ ዋንጫ ሐ. በዝላይ መ. በወርቅ ሜዳሊያ

3. በአንድ የኦሎምፒክ መድረክ ድርብ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት መሆንን ለዓለም ያስተማረው አትሌት ማን ነው?

   ሀ. ኃይሌ ገ/ስላሴ ለ. አበበ ቢቂላ ሐ. ምሩፅ ይፍጠር መ. ቀነኒሳ በቀለ

4. በአዲስ አበባ ከተማ በስሟ ሆስፒታል የተሰየመላት አትሌት ማን ናት?

   ሀ. መሰረት ደፋር ለ. ደራርቱ ቱሉ ሐ. ፋጡማ ሮባ መ. ጥሩነሽ ዲባባ

5. በአቴንስ ኦሎምፒክ በ5ሺ ሜትር 1ኛ በመሆን ወርቅ የተሸለመች አትሌት ማን ናት?

   ሀ. መሰረት ደፋር ለ. ጥሩነሽ ዲባባ ሐ. ደራርቱ ቱሉ መ. ብርሃኔ ሀደሬ

---

## ቃላት

ሀ.“የኦሎምፒክ ፈርጦች” በሚለው ምንባብ መሰረት በ “ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ”ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ፈፀመ | ሀ. አጋጣሚ |
| 2. ውድድር | ለ. ጌጥ |
| 3. ድርብ | ሐ. ፉክክር |
| 4. ዕድል | መ. ጀግና |
| 5. ጀብደኛ | ሠ. አከናወነ |
| 6. ፈርጥ | ረ. እጥፍ |

ለ.“የኦሎምፒክ ፈርጦች” በሚለው ምንባብ መሰረት በ “ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ”ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።


| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ድል | ሀ. ጨረሰ |
| 2. በረታ | ለ. ተቀጣ |
| 3. ተሸለመ | ሐ. ዘገየ |
| 4. ፈጠነ | መ. ሽንፈት |
| 5. ጀመረ | ሠ. ደከመ |

---


## ሰዋስው

ሀ.በምሳሌው መሰረት ዋናውን ቃል ከቅጥያዎች ጋር በማጣመር ባለቅጥያ ቃል መስርቱ።

ምሳሌ፡-




1. አባትነት
2. አባታዊ
3. አባቶች




ለ.በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከተዘረዘሩት ቃላት ጋር በማገናኘት ባለቅጥያ ቃላት መስርቱ፡፡ ቅጥያዎችን ከአንድ ጊዜ በላይ መድገም ይቻላል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| - ኣማ | - ነት | - ኦች |
| - ኣዊ | - ዎች | - ኧኛ |

ምሳሌ፡- ሀ. የዋህ =የዋህነት ፣ የዋሆች

ለ. አገር = አገራዊ ፣ አገሮች ፣ አገርኛ

1. ደግ
2. አሸዋ
3. ነገር
4. ድመት
5. ኢትዮጵያ
6. ጫማ
7. በጎ
8. ተራራ
9. ተንኮል
10. ሰማይ

## ጽሕፈት

ሀ.ከዚህ በታች በተሰጧችሁ ቃላት ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡

1. ታዋቂ
2. ጥርጥር
3. ማስመዝገብ
4. አክብሮት
5. መገፋፋት
6. አስደናቂ

ንባብ

## የኢትዮጵያ የስፖርት አባት



ቅድመ ንባብ

ሀ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?
ለ. የምትመለከቱት ፎቶግራፍ የማን ይመስላችኋል?
ሐ. ፎቶውን በማየት ምንባቡ ምን ሊነግራችሁ እንደሚችል ገምቱ?

አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ከእናታቸው ወይዘሮ ሙላቷ ገብረሥላሴ እና ከአባታቸው ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ መስከረም 1 ቀን 1914 ዓ.ም ተወለዱ:: አቶ ይድነቃቸው እንደ ማንኛው ልጅ እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የቄስ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርት ተምረዋል:: በመቀጠልም የፈረንሳይኛ ትምህርትን ደግሞ በአሊያንስ፣ በዳግማዊ ምኒልክና በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤቶች ተከታትለዋል::

በወቅቱም ለእግር ኳስ፣ ለብስክሌትና ለሩጫ ስፖርቶች ልዩ ፍቅር ነበራቸው:: ብስክሌቱንና ሩጫውን ባይገፉበትም እግር ኳሱን ግን በተጫዋችነት፣ በአሰልጣኝነትና በኋላም በአመራርነት እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ ቀጥለውበት ዛሬም ድረስ ስማቸውን ማስጠራት የቻሉበት ስፖርት ሆኖላቸዋል::

ገና በስምንት ዓመታቸው የትምህርት ቤቱ የሕፃናት እግር ኳስ ቡድንን በአምበልነት እየመሩ ተጫውተዋል። በ1924 ዓ.ም ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና የስዊድኑ ንጉሥ ልጅ በተገኙበት መድረክ ይድነቃቸውና የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው የስፖርት ትርዒት አቅርበው ሽልማት ተቀብለዋል። በስምንት ዓመት እድሜያቸው የስፖርት ዓለም ተሳትፎን የጀመሩት ይድነቃቸው በ14 ዓመታቸው የዛሬውን ቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ ቡድንን ተቀላቀሉ።

ይድነቃቸው ለ23 ዓመታት ያህል ለቅዱስ ጊዮርጊስ በመጫወት እስካሁን ድረስ ባለ ክብረ ወሰን ናቸው። ይድነቃቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ በቆዩባቸው ዓመታት ከተጫዋችነት በተጨማሪ አሰልጣኝ ሆነውም አገልግለዋል። በአንድ የውድድር ዘመን ለክለቡ 43 ግቦችን ማስቆጠር ችለዋል። ይህ ስኬትም ይድነቃቸውን እስካሁን ድረስ ባለክብረወሰን አድርጓቸዋል። የተጫዋችነት ዘመናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ አሰልጣኝነት በመሸጋገር የኢትዮጵያ ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድንን መርተዋል። ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ አንድ ለእናቱ የሆነውን የአፍሪካ ዋንጫዋን በ1954 ዓ.ም ስታሸንፍ የቡድኑ አሰልጣኝ ይድነቃቸው ተሰማ ነበሩ።

ሀ. በስንት ዓመታቸው ስፓርት ጀመሩ? የት እና በምን የስፓርት ዓይነት?
ለ. አቶ ይድነቃቸው ከእግር ኳስ ተጫዋችነት እና ከአሰልጣኝነት ሌላ ምን የሰሩ ይመስላችኋል?

አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ከተጫዋችነትና ከአሰልጣኝነታቸው ባሻገር ታላላቅ ተግባራትን ያከናወኑትና ታዋቂነትን ያተረፉት የስፖርት ማኅበራትን በማደራጀትና በመምራት ነው። የኢትዮጵያ ስፖርት ጽሕፈት ቤትን አቋቁመው ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት ጥረዋል። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን ሲመሰረትም አስተዋጿቸው እጅግ የጎላ ነበር።

አቶ ይድነቃቸው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ እና የካፍ ፕሬዝደንት ሆነው ተሹመው አገልግለዋል። የበርካታ ሪከርዶች ባለቤት የሆኑት አቶ ይድነቃቸው፤ ከውጭ ሀገራት መንግሥታት ሳይቀር ብዙ ዋንጫዎችን፣ ሜዳሊያዎችንና ሌሎች ሽልማቶችን አግኝተዋል። የኢትዮጵያ ዘመናዊ የስፖርት አባት በመባል የሚታወቁት አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ነሐሴ 13 ቀን 1979 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

(ምንጭ፡- አዲስ ዘመን 79ኛ ዓመት ቁጥር 217፤ 2012ዓ.ም፤ ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ)

### ሀ.<<የኢትዮጵያ የስፓርት አባት" በሚለው ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. አቶ ይድነቃቸው ተሰማ በስንት ዓመተ ምህረት ተወለዱ?
2. ምንባቡ ስንት አንቀጾች አሉት?
3. ከእግር ኳስ ተጫዋችነት በተጨማሪ በምን፤ በምን ኃላፊነት ላይ እንደሰሩ ዘርዝሩ?
4. አቶ ይድነቃቸው ተሰማ በቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ቡድን እስከ ስንት ዓመታቸው ድረስ ተጫወቱ?
5. በስንት ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ?

## ቃላት

### ሀ.በምሳሌው መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺቸውን ጻፉ።

| | ቃላት | ተመሳሳይ ፍቺ | ተቃራኒ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ | አሸነፈ | ድል አደረገ | ተሸነፈ |
| 1 | ሁልጊዜ | | |
| 2 | መፈለግ | | |
| 3 | በፊት | | |
| 4 | መዘዋወር | | |
| 5 | ማግኘት | | |
| 6 | ውጤት | | |

### ለ.በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቻቸውን ምረጡ፡፡

1. እኛ ተማሪዎች ጥሩ ባህሪ ልናዳብር ይገባል፡፡
   ሀ. ጠባይ ለ. ኅበዝ ሐ. ባህል መ. ልምድ
2. በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ትምህርታዊ ውድድር ያስደስታል፡፡
   ሀ. ሩጫ ለ. መዋደድ ሐ. ፉክክር መ. መውደድ
3. ኢትዮጵያ የሰው ዘር ማዕከል ናት፡፡
   ሀ. እናት ለ. ዓይነት ሐ. አዋቂ መ. መገኛ
4. ሰዎች በመልካም ስራቸው ሲመሰገኑ በመጥፎ ተግባራቸው ደግሞ ይኮነናሉ፡፡
   ሀ. ይናዘዛሉ ለ. ይወገዛሉ ሐ. ይሸለማሉ መ. ይሾማሉ
5. ባለንጀራን እንደራስ መውደድ ይገባል፡
   ሀ. ቤተሰብን ለ. ዘመድን ሐ. ጓደኛን መ. ጎረቤትን

---

አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ፡፡

## አንድ ብልህ ዐይነ-ስውር

አንድ ዐይነ-ስውር ገንዘብ አጠራቅሞ ማስቀመጫ ስላጣ አንድ ቀን በሌሊት ተነሳና በከረጢት አድርጎ በአትክልቱ ስፍራ ቀበረው፡፡ ይሁን እንጂ ጎረቤቱ ሲቀብረው አይቶት ነበርና ወሰደበት፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ዐይነ-ስውሩ ገንዘቡን ከቀበረበት ለማውጣት ወደ አትክልት ስፍራው ሄዶ ቢፈልገው አጣው፡፡ ጎረቤቱንም ጠረጠረውና በታማኝነት አስመስሎ “ከዚህ በፊት በአትክልቴ ስፍራ ገንዘብ ቀብሬ ነበር፤ አሁንም አንድ ሰው የተበደረኝን ወርቅ መለሰልኝ ስለዚህ የት ባደርገው የሚሻል ይመስልሃል?« ሲል ጠየቀው፡፡ ጎረቤቱም ሁሉንም ለመውሰድ ስለፈለገ “በአንድነት ቅበረው፡፡» አለው፡ ከዛም ጎረቤቱ ለብቻው ሲያስብ ቆየና “በፊት የቀበረውን ገንዘብ ከቦታው ሲያጣው ይህን አሁን ሊቀብረው ያሰበውን ወርቅ አይቀብርም ” ብሎ በማሰብ ሁሉንም በአንዴ ለመውሰድ ሲል የሰረቀውን ገንዘብ ከነከረጢቱ ወስዶ መልሶ እዛው ቦታ ቀበረው፡፡ ዐይነ-ስውሩም በሌሊት መጥቶ ጎረቤቱ መልሶ የቀበረውን ገንዘብ አውጥቶ በምትኩ አንድ ከረጢት ቀበረና ሄደ፤ ጎረቤቱም ተጠባብቆ ቢያወጣው ጠጠር ሆኖ አገኘው፡፡

---

## ሰዋስው

ሀ.የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ስም ወይም ግስ መሆናቸውን በመለየት በየምድባቸው ስር ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| መምህር | መጣ | ቤት | ተማረ |
| ሠራ | ኢትዮጵያ | ተጫወተ | ትምህርትቤት |
| ተማሪ | ተሳፈረ | ዝንጀሮ | ገነባ |
| ነዳ | አደባባይ | ሄደ | ወቀጠ |
| መጽሐፍ | አነበበ | ህንጻ | መኪና |

| | ስም | ግስ |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ቤት | መጣ |
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |
| 8 | | |
| 9 | | |

ለ.በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ባለቤት የሆነውን ቃል ለይታችሁ አውጡ።

ምሳሌ፡- ሀ. የመምህሮቿን ምክር ትሰማለች። የአረፍተነገሩ ባለቤት = እሷ

ለ. ውሻው ስጋ በላ። የአረፍተነገሩ ባለቤት = ውሻው

1. ልጁ መኪና አጠበ።
2. ተማሪዎቹ ጎበዞች ናቸው።
3. ኳስ መጫወት እፈልጋለሁ።
4. ችግኞችን መትከል አለብን።
5. ናትናኤል መጽሐፍ ማንበብ ይወዳል።
6. አህያዋ ድምጿን ከፍ አድርጋ አናፋች።

---

ሐ.በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ተሳቢ የሆነውን ቃል ለይታችሁ አውጡ።

ምሳሌ፡- ሀ. ተማሪዎች ችግኝ ተከሉ። የአረፍተነገሩ ተሳቢ = ችግኝ

ለ. ፖሊስ ወንጀለኛውን ያዘ። የአረፍተ ነገሩ ተሳቢ = ወንጀለኛውን

1. እሱ ወንበሩን ሰበረው።
2. አፎሚያ ጥርሷን ቦረሸች።
3. ድመቷ አይጧን ያዘች።
4. ኃይሉ በሩን ዘጋ።
5. ራህመት ወንድሟን መከረች።

---

መ.በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ግስ(ማሰሪያ አንቀጽ) የሆነውን ቃል ለይታችሁ አውጡ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. እናቴ ከጎረቤቶቻችን ጋር ቡና ትጠጣለች፡፡

የአረፍተነገሩ ግስ(ማሰሪያ አንቀጽ) = ትጠጣለች

ለ. አካባቢያችን ውብ እና ጽዱ ነው፡፡

የአረፍተ ነገሩ ግስ(ማሰሪያ አንቀጽ) = ነው

1. ሰላም በሚኒ ሚዲያ ክበብ ትሳተፋለች፡፡
2. ናሆም መምህሩን አመሰገነ፡፡
3. ሽማግሌዎች የተጣሉትን አስታረቁ፡፡
4. እታፈራሁ ቁርሷን በላች፡፡
5. አናናራችን አብሮነትን ያበረታታል፡፡
6. የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡

---

ሠ.በምሳሌው መሰረት ዓረፍተነገሮቹ ስህተት ካለባቸው በሳጥኑ ውስጥ የ"x" ምልክት፤ ትክክል ከሆኑ የ"√" ምልክት በማድረግ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. አንበሳ የዱር እንስሳ ናቸው፡፡ [x]

ለ. የአካባቢያችንን ንጽህና በጋራ አንጠብቅ፡፡ [√]

1. ዋልያ የኢትዮጵያ ብርቅዬ እንስሳ ነው፡፡ [ ]
2. የሽክላ ስራ የዕደ ጥበብ ማሳያችን ነው፡፡ [ ]
3. በባቡር ተሳፍሬ ወደ ቃሊቲ ሄደ፡፡ [ ]
4. ኪስ ሲጫወት እግሩን ተሰበረች፡፡ [ ]
5. መርካቶ ከአፍሪካ ትልቁ የገበያ ማዕከል ነው፡፡ [ ]

---

## ጽሕፈት

### ሀ.በምሳሌው መሰረት የባለቤት እና የግስ ስምምነት ስህተቶችን በማስተካከል ዓረፍተነገሮቹን በድጋሚ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ሀ. እኔና አባቴ እንጦጦ ፓርክን ጎበኘ።

✓እኔና አባቴ እንጦጦ ፓርክን ጎበኘን።

1. ሀኪሞች ሕሙማንን ትንከባከባለች።
2. በአቅራቢያችን ትምህርት ቤቶች ይገኛል።
3. ሁላችንም ቡና ጠጣሁ።
4. በተሰማራበት ስራ ስኬታማ ሆኑ።
5. ቤቶቹ ተመልሶ ተገነባ።
6. ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚሶች ይበጣጠስ።
7. እኔ ዳቦ ለመግዛት ሄድን።
8. ኢትዮጵያ 3ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ አሸንፈዋል።

---

## መናገር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ተዘጋጅታችሁ ውይይት አድርጉ።

የመወያያ ርዕስ

- መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ርዕስ መሰረት ስለ አገራችን ታዋቂ አትሌቶች በሰበሰባችሁት መረጃ መሰረት ውይይት አድርጉ።

  ምሳሌ፡-

ሀ. አትሌት አበበ ቢቂላ

ለ. አትሌት ስለሺ ስህን

ሐ. አትሌት ፋጡማ ሮባ

መ. አትሌት ጌጤ ዋሚ

ሠ. አትሌት ሚሊዮን ወልዴ

ረ. አትሌት ለተሰንበት ግደይ

## የምዕራፍ ስድስት የክለሳ ጥያቄዎች

1. የውይይት ምንነትን ከክርክር ጋር በማነጻጸር አብራሩ?

2. ከሚከተሉት ባለቅጥያ ቃላት ውስጥ ቅጥያዎችን በመነጠል ጻፉ?

| ተ.ቁ | ባለቅጥያ ቃላት | ዋና ቃል | ቅጥያ |
|---|---|---|---|
| 1 | ማንኪያዎች | | |
| 2 | ወላጆች | | |
| 3 | ሰንሰለታማ | | |
| 4 | ህዝባዊ | | |
| 5 | ጥፋተኛ | | |

3. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ?

| ተ.ቁ | ቃላት | ተመሳሳይ ፍቺ | ተቃራኒ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| 1 | በረታ | | |
| 2 | ተሸፈነ | | |
| 3 | ግልጽ | | |
| 4 | ፈጣን | | |
| 5 | ገነባ | | |

4. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሳሳተውን የባለቤት እና የግስ ስምምነት አስተካክላችሁ ጻፉ?

ሀ. የኢትዮጵያውያን የቀን አቆጣጠር ከሌሎች ተለየች፡፡

ለ. በአዲስ አበባ ውስጥ በርካታ ሰዎች ኖረ፡፡

ሐ. ስፓርት ለጤና ጠቃሚ ናቸው፡፡

አማርኛ
፬ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሰባት
## ውሃ

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ኢ-መደበኛ በሆነ አደረጃጀት በሚና ጨዋታ ውስጥ ትሳተፋላችሁ፡፡
- አዳምጣችሁ የጽሁፉን ሃሳብ በዝርዝር ትገልጻላችሁ፡፡
- በራሳችሁ አገላለጽ ዓረፍተ ነገሮች ትመሰርታላችሁ፡፡
- ገላጮችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮች ትመሰርታላችሁ፡፡
- መዝሙር አዳምጣችሁ ስለ ውሃ ጥቅም ትጽፋላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ርዕስ ክርክር ታደርጋላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ግስ የተሟላ አረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### ውሃ ምንድን ነው?



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. ውሃ ከምን፣ ከምን የሚገኝ ይመስላችኋል?
ለ. ውሃን በቤታችሁ ውስጥ ለምን፣ ለምን ተግባራት እንደምትጠቀሙበት በዝርዝር ተናገሩ?
ሐ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን ጉዳዮች የሚያነሳ ይመስላችኋል፡፡

ሀ."ውሃ ምንድን ነው?" በሚለው ምንባብ መሰረት የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት በቃል መልሱ። ለመልሶቻችሁም ማብራሪያ ስጡ።

1. ውሃ ለሰው ልጅ እንጂ ለእንስሳትና ለእፅዋት አስፈላጊ ነገር አይደለም።
2. ውሃ ለምግብ ማብሰያነት እና ለመጓጓዣነት ብቻ ያገለግላል።
3. ንጹህ ውሃ በውስጡ ሌሎች ነገሮችን ማሳየት ይችላል።
4. በውቅያኖስና ከባህር የሚገኝ ውሃ ለመጠጥ አገልግሎት ይውላል።

---

ቃላት

ሀ. በዓረፍ ተነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ከተሰጡት አማራጮች መካከል አገባባዊ ፍቻቸውን የሚያሳይ ቃል ምረጡ።

1. ወፏ ከዛፎቹ መሃል ካለው ኩሬ ላይ ስትንቦጫረቅ አየሁ።

   ሀ. ወንዝ ለ. ምንጭ ሐ. ያቆረ ውሃ መ. ባህር

2. ኢትዮጵያ በበርካታ መዓድናት የከበረች ዓገር ናት።

   ሀ. ንጥረ-ነገሮች ለ. ባህሎች ሐ. ባህር መ. ምግብ

3. ውሃ መያዣ ያስፈልገዋል።

   ሀ. ማፍሰሻ ለ. ማንቀሳቀሻ ሐ. ማንጠልጠያ መ. ማጠራቀሚያ

4. ውሃ ህይወት ላላቸው ነገሮች በሙሉ በመሰረታዊነት ያስፈልጋል።

   ሀ. በአማራጭነት ለ. በዋናነት ሐ. በተጨማሪነት መ. በትርፍነት

---

ለ. በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ይከፈላል | ሀ. ማጣት |
| 2. ማግኘት | ለ. ጠጣር |
| 3. ፈሳሽ | ሐ. ይጎዳል |
| 4. መያዝ | መ. ይገናኛል |
| 5. ያገለግላል | ሠ. መልቀቅ |

ሐ.በምሳሌው መሰረት ከተሰጣችሁ ቃላት ውስጥ ሌሎች ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| አስቀሰበት | አለቀ | አለት |
| | ሰቀለ | በሰለ |
| | አለ | ቀለበት |

1.

| | | |
|---|---|---|
| መመጣጠናቸው | | |
| | | |
| | | |

2.

| | | |
|---|---|---|
| ስለመሰከረለት | | |
| | | |
| | | |

3.

| | | |
|---|---|---|
| አመስቃቀለ | | |
| | | |
| | | |

4.

| | | |
|---|---|---|
| አሰባበረ | | |
| | | |
| | | |

## መናገር

ሀ.መምህራችሁ “ጤናችን በእጃችን” በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን ግጥም በማድመጥ በዜማ በሉ፡፡

ለ.መምህራችሁ በሚሰጧቹ ትዕዛዝ መሰረት የመዝሙሩን መልዕክት በራሳችሁ አገላለጽ በአራት ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ሐ.በቡድን በመሆን ስለ ውሃ አጠቃቀም የተመለከተ አጭር ጭውውት ወይም መዝሙር አዘጋጅታችሁ በድራማ መልክ አቅርቡ፡፡

## ጽሕፈት

ሀ. የሚከተሉትን የተዘበራረቁ ዓረፍተነገሮች ቅደም ተከተላቸውን በማስተካከል አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ለ. ከእነዚህ ተግባራት መካከል በጠዋት ተነስታ አልጋዋን ካነጠፈች በኋላ ፊቷን በውሃ እና በሳሙና ትታጠባለች፡፡

ሐ. ብሌን ዘወትር ትምህርት ቤት ከመሄዷ በፊት የተለያዩ ተግባራትን ታከናውናለች፡፡

መ. ከዛም የደንብ ልብሷን ለብሳ የተዘጋጀላትን ቁርስ ትበላለች፡፡

ሠ. እሷም ወደ ትምህርት ቤት ትገባለች፡፡

ረ. ቀጥሎም ማታ ላይ ያዘጋጀችውን ደብተሮች በቦርሳ ይዛ እናቷን ተሰናብታ ከአባትዋ ጋር ጉዞ ትጀምራለች፡፡

ሰ. አባቷም ትምህርት ቤቷ በር ላይ እንዳደረሷት ተሳስመው ተለያዩ፡፡

### መነሻ፡-

ብሌን ዘወትር ትምህርትቤት ከመሄዷ በፊት የተለያዩ ተግባራትን ታከናውናለች፡፡

## ንባብ

### ከሰከላ እስከ ጉባ



## ቅድመ ንባብ

ሀ. የህዳሴው ግድብ እየተገነባ ያለበት ክልል እና ልዩ ቦታ ስም ታውቃላችሁ?
ለ. ስለአባይ ወንዝ የምታውቁትን በዝርዝር ተናገሩ?
ሐ. የአባይ ወንዝ መነሻ ቦታ ማን ይባላል?

የአባይ ወንዝ በአገራችን መልክዓ-ምድር ምዕራብ ጎጃም ዞን ልዩ ስሙ ሰከላ ከሚባል አካባቢ ፈልቆ ጣናን መነሻ አድርጎ ሌሎች ገባር ወንዞችም አብረውት ተቀላቅለው እንዲጓዙ በማድረግ ያለከልካይ ለአያሌ ምዕተ-ዓመታት ለም አፈራችንን እየጠራረገ ለጎረቤት አገራት ሲሳይ በመሆን ለሃገራችን ምንም ጥቅም ሳይሰጥ ቆይቷል።

የአባይን ወንዝ መጠን እየጨመሩና እያበዙ ከሚሄዱ በርካታ ገባር ወንዞች መካከል

ወንቃ፣ ጀማ፣ ሙገር፣ ጉደር፣ ደዴሳ፣ ነዲ፣ ዳቡስ፣ ቱሉ፣ አባያ፣ ሙጋ፣ ሱሃ፣ ጉላ፣ ተምጫ፣ ባጫት፣ ጨሞጋ፣ በለሳ፣ ጉማራና ዋቤ ይጠቀሳሉ፡፡ አባይ ዛሬ ላይ ግን እንደ ትናንቱ ሳይሆን ዓይኑን ወደ እናቱ፣ ልቡን ወደ ትውልድ አገሩ፣ እግሩን ወደኋላ ለማዞር የሩጫ መንገዱን ለመግታት ከጉባ ሰማይ ስር አለኋችሁ ብሏል፡፡ አባይ ከጉባ ሰማይ ስር በጭስ ብዛት የዛሉ ዓይኖች የሚጠብቁት፣ ብርሀን ፈላጊ ዜጎች ተስፋ የሚያደርጉት፣ የአይበገሬነታችን ማሳያ፣ የተፈጥሮ ልግስናችንና የኢትጵያዊነት የክብራችን ግርማ ሞገስ የሆነ ታላቅ ወንዝ ነው፡፡

ሀ. "አባይ ዛሬ ላይ አይኑን ወደ እናቱ አዙሯል፡፡" ሲል ምን ማለቱ ነው?
ለ. የአባይ ወንዝ መገደቡ  ምን ጥቅም ይሰጣል?

በዚህ ታላቅ ወንዝ ላይ ለዘመናት ኢ-ፍትሐዊ ፍርድ ተፈርዶብን የ86 በመቶ የውሃ አመንጭነት ድርሻችን ሳይታይ፤ አይችሉትም ሲሉ ችለን ይህን ታላቁን የህዳሴ ግድብ በመገደብ በኃይል ማመንጫነትና ፈርጀ ብዙ የልማት ጎዳናዎችን የሚያቀናጅ ግዙፍ ተግባር ሆኗል፡፡ ይህ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ካለው ፈርጀ ብዙ ጥቅም በዋናነት የሚጠቀሰው የአገራችንን የኃይል ፍላጎት ከማሟላት አልፎ ለጎረቤት አገራት ፍትሀዊነት ባለው መልኩ በመሸጥና አብሮ በመልማት በሚደረገው የመደጋገፍ ጉዞ ነው፡፡ በተለይም ለምስራቅ አፍሪካ የኃይል ትስስር በመፍጠር ያለንን የኢኮኖኮሚና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ከፍ እንዲል ከማስቻሉም በላይ እንደ አህጉርም ለአፍሪካ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

ግንባታው እየተካሄደ ያለው በኢትዮጵያ ምድር ከራስ አብራክ በሚፈልቅ ወንዝና በራስ ወጪ በመሆኑ የዘመናት ቁጭታችንን የሚሽር፣ የአብሮነታችንና የመተባበራችን ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ገፀ-በረከት የሆነውን  የአባይ ውሃ ጥቅም ላይ ለማዋል ታልሞ በሚሰራው ስራ የኢትዮጵያዊያን ኩራት በሆነው ታላቁ የህዳሴ ግድብ የኃይል ማመንጫ ላይ ትልቅ ተስፋ ሰንቀንበታል፡፡ ይህ ከድህነት መላቀቂያ የሆነው የሰንደቅ አላማ ፕሮጀክታችን ያለምንም ብድርና እርዳታ በኢትዮጵያዊያን ርብርብ ተገንብቶ በቅርብ ይጠናቀቃል፡፡ በዚህም እኛ የአባይ ዘመን ልጆች ልንኮራ ይገባል፡፡

(ምንጭ፡- ኢ.አ.ከ አስተዳደር፤ ዝክረ ህዳሴ በአዲስ አበባ፤2013 ዓ.ም፤ ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

ሀ. “ከሰከላ እስከ ጉባ” በሚለው ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

1. የአባይን ወንዝ መጠን እንዲጨምር የሚያደርጉ ገባር ወንዞችን ዘርዝሩ?
2. የህዳሴ ግድብ እየተገነባ ያለው በማን ወጪ ነው?
3. “የአባይ ግድብ የአይበገሬነታችን ማሳያ ነው፡፡” ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ይህን ታሪካዊ ግድብ ለማጠናቀቅ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
5. የአባይ ወንዝ ግድብ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር ያለንን ግንኙነት በምን መልኩ እንደሚያጠናክር አብራሩ?

---

## ቃላት

ሀ. ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ተቀላቅለው
2. አያሌ
3. መግታት
4. ዛለ
5. ጥቅም

---

ለ.በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቻቸውን ምረጡ፡፡

1. እኛ ኢትዮጵያዊያን ኩሩ ነን፡፡

ሀ. አንገት ደፊ ለ. ልበ-ቢስ ሐ. ጉረኛ መ. ልበ-ሙሉ

2. የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፋይዳ የጎላ ነው፡፡

ሀ. አስፈላጊ ለ. ጥቅም ሐ. ጥናት መ. ጉዳት

3. የኤሌክትሪክ ኃይል ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡

ሀ. በርካታ ለ. የመብራት ሐ. ጥቂት መ. መጠነኛ

4. የአባይን ወንዝ መጠን እየጨመሩ የሚሄዱ በርካታ ገባር ወንዞች አሉ፡፡

ሀ. ጥቂት ለ. ረጃጅም ሐ. መጋቢ መ. በርካታ

5. የምዕተ- ዓመቱ ትልቅ ስራ በአባይ ወንዝ ላይ እየተሰራ ነው፡፡

ሀ. የመቶ ዓመቱ ለ. የሃምሳ ዓመቱ ሐ. የሺህ ዓመቱ መ. የአስር ዓመቱ

6. ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በቅርቡ <u>ይቋጫል</u>፡፡

ሀ. ይሰፋል ለ. ይጀመራል ሐ. ይጠናቀቃል መ. ይቀጥላል

7. ወንዞቻችን <u>ግርማ ሞገስ</u> ናቸው፡፡

ሀ. ፏፏቴ ለ. ኃይል ማመንጫ ሐ. ማስፈራሪያ መ. ኩራት

---

## ጽሕፈት

### ሀ.በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮች መስርቱ፡፡

1. ትስስር
2. አብራክ
3. ሰንቀን
4. ሲሳይ
5. ዘመናት

---

## ንግግር

### ሀ.መምህራችሁ በሚሰጧችሁ የመከራከሪያ ርዕስ መሰረት አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ እና የክርክር መመሪያ በመከተል ክርክር አከናውኑ፡፡

## ሰዋስው

---

### ሀ.በምሳሌው መሰረት ለሚከተሉት ያልተሟሉ አረፍተነገሮች ተገቢውን ገላጭ ቃላት በመጠቀም አሟሉ፡፡

1. ሪቻርድ ፓንክረስት <u>ኢትዮጵያዊ</u> ዜግነት አግኝተዋል፡፡
2. እሱ____________ተማሪ ነው፡፡
3. እናቴ ____________________የባህል ልብስ ለብሳለች፡፡
4. አዳራሹ______________ስለሆነ ብዙ ሕዝብ ይይዛል፡፡
5. __________ልጅ መጣ፡፡

6. __________አባት አለኝ፡፡
7. __________ ህዝብ ተሰበሰበ፡፡
8. _______________ውሃ በባልዲ ቀዳሁ፡፡
9. _______________ተማሪ የግል ንጽህናውን አይጠብቅም፡፡
10. ቁመቱ______________________ስለሆነ መሰላሉ ይሉታል፡፡

---

ለ. ከዚህ በታች የቀረቡት ገላጭ ቃላት በዓረፍተነገር ውስጥ በመጠቀም አሳዩ፡፡

1. ቀይ
2. ትልቅ
3. አጭር
4. ጨካኝ
5. ሁለት
6. ሩህሩህ

---

ሐ. ከዚህ በታች በሳጥኑ ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላቶች መካከል ግስ የሆኑትን ብቻ መርጣችሁ ጻፉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ተነሳ | ሰንደቅ-ዓላማ | ጥቁር | አነበበ |
| አንበሳ | አደገ | ቆረጠ | የዋህ |
| ነው | ጠማማ | መምህር | ቀባች |
| ለስላሳ | አሸነፈ | አጸዳ | ኢትዮጵያ |
| ሮጠ | ክብ | አፈር | አበሰ |

ምሳሌ፡- ተነሳ

---

## ጽሕፈት

### ሀ.ከዚህ በታች ያልተጠናቀቁ ዓረፍተነገሮችን በተገቢው ግስ አሟልታችሁ ጻፉ።

1. መስከረም ሲጠባ አደይ አበባ ________________።
2. የመጀመሪያዋ ሴት አውሮፕላን አብራሪ ካፒቴን ሙሉእመቤት እምሩ ______።
3. ኢትዮጵያ የገጠሟትን ጠላቶች ከእግሯ ስር________________።
4. እጃችንን በውሃና በሳሙና መታጠብ____________።
5. ትምህርት ለአገር ዕድገት መሰረት______________።
6. የኮሮና ቫይረስ በሽታን ለመከላከል አካላዊ ርቀታችንን _____________።
7. በአዲስ አበባ በርካታ ቋንቋዎች _______________።
8. በትምህርት ቤታችን ጠዋት፤ ጠዋት ብሔራዊ መዝሙር _________።

---

### ለ. ከታች በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ስድስት ግሶችን ካወጣችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገሮች ስሩባቸው።

አንድ ባልና ሚስት ነበሩ። ባልየው ቀኑን ሙሉ ከሐይቅ ውስጥ ዓሣ ያጠምዳል፡ ሚስትየው አሳዎቹን ትሸጣለች፤ ሆኖም የዓሣ ገበያ ብዙም አስደሳች አይደለም። ስለዚህ ገቢያቸው አነስተኛ ነበር። ቢሆንም ግን ሁልጊዜ የበለጠ ይጥራሉ።

---

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ ምንባብ አንብቡ

ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ

### አህያ እና በሬ

አንድ ገበሬ ሁለት በሬዎች እና አንድ አህያ ነበሩት፡፡ አንደኛው በሬ በጣም ከስቶ ነበር፡፡ አህያው ደግሞ በጣም ወፍሮ ነበር፡፡ አህያው አንድ ቀን በሬውን "ምነው ሰውነትህ ከሳ?" ሲል ይጠይቀዋል፡፡ በሬውም "እርሻ ስለበዛብኝ፣ እረፍትና በቂ ሳር ስላጣሁኝ ነው፡፡" አለው፡፡ አህያውም ያዝንና፤ "አሞኛል ብለህ ተኛና ትንሽ ቀን እረፍ፡፡" አለው፡፡ በሬውም አህያውን "አሁን ገና ጥሩ ምክር መከርከኝ፡፡" አለና ፣ ወዲያውኑ እያነከሰ ወደቤቱ ሄደ፡፡

ባለቤቱም በእርሻ ወቅት በሬው በማንከሱ በጣም አዘነ፡፡ ቶሎ እንዲድንለት ሳር እና ውሃ ይሰጠው ጀመር፡፡ ከእርሻውም እንዲያርፍ አድርገው፡፡ እስከዚያው ድረስ ግን አህያውን ከሌላኛው በሬ ጋር ጠምዶ እርሻውን ያርስ ጀመር፡፡ አህያው ግን እንደ በሬው ሊያርስለት አልቻለም፡፡ ስለዚህ ይናደድና ጀርባው እስኪመለጥ ድረስ በጅራፍ ሲገርፈው ይውላል፡፡ እረፍት ሲያደርግ፣ ሲበላና ሲተኛ የዋለው በሬ አህያው ከእርሻ ሲመለስ ያገኘዋል፡፡ "አህያ፤ እንዴት ዋልክ?" አለው፡፡ አህያውም "እኔስ ደህና ውያለሁ፤ ለመሆኑ አንተ እንዴት ዋልክ?" ሲል መልሶ ይጠይቀዋል፡፡ በሬውም "የኔን ነገር ተወው ባክህ እጅግ በጣም አሞኝ ዋለ፡፡" አለው፡፡ ከዚያም በሁኔታው የተናደደው አህያ ፣ "አይ!. . .መታመምህስ ባልከፋ" ይለዋል፡፡ "እንዴት?" ሲል በሬው አህያን በድንጋጤ ይጠይቃል፡፡ "እንዲያው አንድ አስደንጋጭ ነገር ሰምቼ በጣም አዘንኩ፡፡" አለው፡፡ አያ በሬም "ምን ሰማህ?" ይላል፡፡ "ይኸ በሬ ቶሎ የማይድን ከሆነ፤ ሰውነቱ ይበልጥ ከመክሳቱ በፊት አርደን ስጋውን እንካፈለው እያሉ ሲማከሩ ሰማሁ፡፡" አለው፡፡ በሬውም በሰማው ነገር ይደናገጥና ማንከሱን አቁሞ፣ እያገሳና እየፈነጠዘ ወደቤቱ ሄደ፤ ይባላል፡፡

(ምንጭ፡- ባዩ ይማም፣ 2002፣አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፣ከገፅ 101-102 ለንባብ ማስተማሪያነት ተሻሽሎ የቀረበ)

## የምዕራፍ ሰባት የክለሳ ጥያቄዎች

1. አምስት የተለያዩ ገላጭ ቃላትን በዓረፍተነገሮች ውስጥ በመጠቀም አሳዩ፡፡
2. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ጻፉ፡፡

   1. ዛለ
   2. ለገሰ
   3. የራስ አብራክ
   4. ህቡዕ
   5. ደባ
   6. ነፈገ

3. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

   1. ዕድገት
   2. የግል
   3. ታላቅ
   4. ፈሪ
   5. ክብር
   6. መሸጥ

4. ከሚከተሉት የቃላት ዝርዝር ውስጥ ግሶችን ብቻ በመምረጥ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሙልሙል | ደማቅ | ተሳተፈ | ጠመኔ | መርካቶ |
| ቻለ | ወረቀት | አስተዋይ | አከናወነ | ስስ |
| ውሃ | አደገ | ከተማ | ጸጉራም | አዳበረ |

አማርኛ
፬ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስምንት
## መደራደር

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ

ተማሪዎች፡-

- አዳምጣችሁ ተራ በተራ በንግግር ትሳተፋላችሁ፡፡
- በግላችሁ አንብባችሁ ዝርዝሩን ታብራራላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤታችሁን ህግና ደንብ ትጽፋላችሁ፡፡
- ቅጥያዎችን ከቃላት ላይ ትነጥላላችሁ፡፡



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን የሚያነሳ ይመስላችኋል?
ለ. ሰዎች ሲደራደሩ አይታችሁ ታውቃላችሁ?

ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በቃል ስጡ፡፡

1. ኑሃሚን ሊቀ-ትሁት የሚል ቅፅል ስም የተሰጣት በምን ምክንያት ነው?
2. ኑሃሚን በምታገኘው አጋጣሚ ሁሉ የምታስተምረው ስለምን ጉዳይ ነው?
3. ሁለት ተማሪዎች ለድብድብ ሲጋበዙ ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ከድርድሩ በመነሳት ከሁለቱ ጓደኛሞች ጥፋተኛው ማነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ምክንያታችሁን ተናገሩ?
5. ከምንባቡ ምን መልዕክት አገኛችሁ?

## ቃላት

ሀ. በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ፍርድ | ሀ. አላስፈላጊ |
| 2. ትሁት | ለ. ሰበብ |
| 3. አልባሌ | ሐ. አየች |
| 4. ተመለከተች | መ. ቅን |
| 5. ምክንያት | ሠ. ብይን |

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

1. ልዩነት
2. መፍታት
3. ጸብ
4. ሩቅ
5. መውሰድ
6. መነሻ
7. ማጠናቀቅ

### ሐ. ለሚከተሉት ቃላት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተመሳሳይ ፍቻቸውን ምረጡ፡፡

1. መሰሪ

    ሀ. ተንኮለኛ ለ. ወረኛ ሐ. ወረተኛ መ. ሰራተኛ

2. ልፍስፍስ

    ሀ. ጠንካራ ለ. የሚለፋ ሐ. አቅመቢስ መ. ብርቱ

3. ዘለፋ

    ሀ. ምርቃት ለ. ስድብ ሐ. ዘፈን መ. ስልጣን

4. ተለጠጠ

    ሀ. ተዘረጋ ለ. ተጣጠፈ ሐ. ታጠፈ መ. ተዘነጋ

5. ማዋሃድ

    ሀ. ማደባለቅ ለ. አንድ ማድረግ ሐ. መቀላቀል መ. ሁሉም

---

### መ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በማጥበቅ እና በማላላት ሲነበቡ የተለያየ ትርጉም የሚሰጡ ቃላትን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- እንጨቱን ጥፍር አድርጎ አሰረው፡፡ ጥፍር ሲጠብቅ = ጥብቅ ማድረግ

ሲላላ = የአካል ክፍል

1. ወደ ትምህርትቤት ከመሄዱ በፊት ቁርሱን በላ፡፡

2. ነስረዲን ከተቀመጠበት ቀና ብሎ መጻፍ ጀመረ፡፡

3. የአማርኛ መጽሀፍ አለኝ፡፡

4. መብራቱ በራ፡፡

---

## ጽሕፈት

ሀ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገሮች ስሩባቸው፡፡

1. አመራች
2. መገልገል
3. ይማሩበታል
4. ባለጋራ
5. ወዳጅ

---

## መናገር

ሀ.መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ርዕስ ላይ ዝግጅት በማድረግ እና የንግግር ሕጎችን በመከተል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ፡፡

---

## ንባብ

### ድርድር



## ቅድመ ንባብ

ሀ. ድርድር ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?
ለ. ሱቅ ተልካችሁ እቃ ተደራድራችሁ ገዝታችሁ ታውቃላችሁ? እንዴት እንደነበር ተናገሩ፡፡
ሐ. ምንባቡ ስለምን የሚናገር ይመስላችኋል?

ወይዘሮ የኔነሽ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ልጅ አለቻቸው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ለትምህርቷ የሚሆን አጋዥ መፅሐፍ ሊገዙላት በአካባቢያቸው ወደሚገኝ የመፅሐፍት መደብር አቀኑ፡፡ ከ15 ደቂቃ የእግር ጉዞ በኋላ ከአንድ የመፅሐፍት መደብር ውስጥ ገብተው መጣራት ጀመሩ፡፡

ወ/ሮ የኔነሽ ፡- ባለ ሱቅ! ኧረ ባለ ሱቅ !

ባለመደብር ፡- አቤት ! ምን ልስጥዎት?

ወ/ሮ የኔነሽ ፡- ለ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አጋዥ መፅሐፍ ፈልጌ ነበር፡፡

ባለመደብር ፡- "የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አጋዥ መፅሐፍ" የሚል አለ፡፡ ይኸው፡፡

ወ/ሮ የኔነሽ ፡- ዋጋው ስንት ነው?

ባለመደብር ፡- ዋጋው 80 ብር ብቻ፡፡

ወ/ሮ የኔነሽ ፡- እያገላበጡ እያዩት እንዴ! ቀንስልኝ እንጂ 80 ብር! ዋጋው በጣም ውድ ነው፡፡

ሀ. ወይዘሮ የኔነሽ መጽሀፍ የሚገዙት ለማን ነው?
ለ. ከዚህ በኋላ ምን የሚገጥማቸው ይመስላችኋል?

ባለመደብር ፡- በቃ ሰባ አምስት ብር ውሰዱት አዲስ መጽሀፍ ነው፡፡ በዛ ላይ መጽሀፉን ሳመጣ የትራንስፖርት ፣ የተሸካሚ ብቻ ብዙ ወጪ አውጥቼበታለሁ፡፡

ወ/ሮ የኔነሽ ፡- ኧረ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ መጨመር ጥሩ አይደለም፡፡ በጅምላ ስታመጡ ቅናሽ እንዳለው እናውቃለን፡፡

ባለመደብር ፡- እሺ በስንት ብር ይገዙኛል?

ወ/ሮ የኔነሽ ፡- እኔ የምገዛው መጽሐፉ ላይ በተቀመጠው የዋጋ መጠን ነው፡፡ ስልሳ ብር፡፡

ባለመደብር ፡-ኧረ ብዙ ወጪ አውጥቻለሁ ባይሆን ሰባ ብር ላድርግሎት፡፡

ወ/ሮ የኔነሽ ፡- ስልሳ ብር ከሸጥክ ሸጥልኝ፤ የማትሸጥልኝ ከሆነ ይቅርብኝ፡፡ ከሸጥክ ይኸው ብሩን ያዝ፡፡

ባለመደብር ፡- እሺ! ባይሆን ለሌላ ጊዜ ደንበኛ እንሆናለን፡፡

ወ/ሮ የኔነሽ ፡- እሺ አመሰግናለሁ! ብለው መጽሀፉን ገዝተው ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡

ወደቤታቸ ሲደርሱ ለልጃቸው መጽሀፉን ሰጧት፤ ልጃቸውም በእናቷ ድጋፍ እጅግ ተደስታ እናቷን አመሰግና፤ መጽሀፉን ማንበብ ጀመረች፡፡

### ሀ.በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

1. ባለመደብሩ "ምን ልስጥዎት" ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ወ/ሮ የኔነሽ ወደ መደብሩ የሄዱት ምን ለማድረግ ነው?
3. ባለመደብሩ መጽሐፉን ከ60 ብር በታች ወይስ በላይ ነው ያመጣው? መልሳችሁን በምክንያት አስረዱ፡፡
4. ወ/ሮ የኔነሽ መጽሐፉን ከ60 ብር በላይ አልገዛውም ብለው በአቋሟቸው እንዲጸኑ ያደረጋቸው ምክንያት ምንድን ነው?

---

## ቃላት

### ሀ.በ"ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አጋዥ | ሀ. ማስተካከል |
| 2. ያልተገባ | ለ. ማገዝ |
| 3. መርዳት | ሐ. ውድቀት |
| 4. ኪሳራ | መ. ረዳት |
| 5. ማቅናት | ሠ. አላስፈላጊ |

---

### ለ.ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

1. ወጪ
2. ውድ
3. መሸጥ
4. መስጠት
5. ጫኝ

---

## ጽሕፈት

### ሀ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮች መስርቱ።

1. ደንበኛ
2. ኪራይ
3. ሱቅ
4. ሽጠ
5. ከፈለ
6. ጨመረ

---

## ሰዋስው

### ሀ. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መጨረሻ ላይ በቅንፍ ውስጥ ከተቀመጡት ቃላት መካከል በመምረጥ የዓረፍተ ነገሩን ሃሳብ አሟሉ።

1. የባቡር__________እየተሰራ ነው። (ሃዲድ/ሃዲዶች)
2. ከኢትዮጵያ ወደ ጎረቤት አገሮች የማይፈስ _ አዋሽ ነው። (ወንዝ/ወንዞች)
3. በግቢያችን ውስጥ በርካታ የጓሮ ___________ተክለናል። (ተክል/አትክልቶችን)
4. መኪና፣ ባቡር እና አውሮፕላን ዘመናዊ ___ናቸው። (መጓጓዣ/መጓጓዣዎች)
5. በበዓል ቀናት የተለያዩ የባህል __________ይለበሳሉ። (ልብስ/ልብሶች)

---

### ለ. በሳጥኑ ውስጥ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አገላለጾች አሟሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| አምቡላ | ላጨ | ተደፋ | ይጣላል |
| ይራመዳል | ገጠመ | አብራሪ | አወጣች |

ምሳሌ:- እንጀራ ተጋገረ ካልን ድፎ ዳቦ_______ተደፋ_____እንላለን።

1. እባብ በልቡ ይሳባል ካልን ሰው በእግሩ_______________እንላለን።
2. ጠላ ይጠመቃል ካልን ጠጅ__________እንላለን።
3. ለቡና እና ለጠላ አተላ ካልን ለጠጅ_____________እንላለን።

4. ጠላ ጠመቀች ካልን አረቄ ____________እንላለን፡፡
5. ለጽሁፍ ጻፈ ካልን ለግጥም____________እንላለን፡፡
6. መኪና አሽከርካሪ ካልን አውሮፕላን____________________እንላለን፡፡
7. ለበግ ጸጉር ሸለተ ካልን ለሰው ጸጉር ____________እንላለን፡፡

---

## ሐ. ከሚከተሉት ባለቅጥያ ቃላት ውስጥ ዋና ቃሉንና ቅጥያውን ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ኢትዮጵያዊ = ኢትዮጵያ- ኣዊ

1. ቦርሳዎች
2. በጎች
3. ልባችን
4. ወንድማችን
5. ምርታማ

---

## መ. ከሚከተለው ሳጥን ውስጥ የመነሻ እና የመድረሻ ቅጥያዎችን የያዙ ቃላትን በየምድባቸው አስቀምጡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| መጣችሁ | እንደተጻጻተ | ደረጃዎች |
| ከህዝብ | ተኛች | የተማሪ |
| አስመከረ | ታሪካዊ | ወጥመዶች |
| ልባም | በቴሌቪዥን | ስለአሁን |

**የመነሻ ቅጥያዎችን የያዙ ቃላት**


1. ከሕዝብ
2.
3.
4.
5.
6.

**የመድረሻ ቅጥያዎችን የያዙ ቃለት**

1. መጣችሁ
2.
3.
4.
5.
6.

---

ሠ.ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ቅጥያዎችን በመጠቀም ባለቅጥያ ቃላትን መስርቱ፡፡





ምሳሌ፡- - ኦች = እርሳሶች

- ኣማ = አፈራማ

---

ረ.የሚከተለውን የቀለም እና የቁጥር ቅደም ተከተል በመከተል የቤተሰብ አቆጣጠርን ተራበተራ በቅደም ተከተልን ጻፉ፡፡


መነሻ




| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማንተቤ | ፍናጅ | ምንዥላት | አስልጥ | ቅም አያት |
| ቅናጅ | አመልጥ | ድርባቴ | ልጅ | ቅድመ አያት (ቅድም አያት) |
| ቅማንት | አያት | እንጅላት | ሽማት | አባት/ እናት |

## ጽሕፈት

### ሀ.በምሳሌው መሰረት ስም፣ ገላጭ እና ግስን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡




ምሳሌ፡- አረንጓዴ ሹራብ ተገዛልኝ፡፡

1.

2.

3.

---

## ንግግር

ሀ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሰረት ስለ ትምህርት ቤታችሁ የተማሪዎች ሕግና ደንብ መረጃ በመሰብሰብ እና ዝግጅት በማድረግ የንግግር መመሪያን ተከትላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ፡፡

---

### አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ፡፡

## ሞኟ አህያ

በድሮ ጊዜ ክፉ ቀን መጣና ፍጥረታት ሁሉ የሚልሱት የሚቀምሱት አጡ። ክፉ ቀኑ የመጣበት ምክንያትም ባለመታወቁ ሁሉም በየፊናው ለማወቅ ይጥር ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን አንበሳ፣ ነብር፣ ጅብ እና አህያ ክፉ ቀን የመጣበትን ምክንያት ለማወቅ ይወያዩ ነበር። በመጨረሻ ግን ከመካከላቸው አንዱ ኃጢአት በመስራት ይሆናል ብለው ስለገመቱ እያንዳንዳቸው የሰሩትን ኃጢአት ሊናዘዙ ተስማሙ። ኃጢአት ሰርቶ የተገኘም ሊፈረድበት ነበር።

በመጀመሪያ አቶ አንበሳ ተናገረ፡- “አንድ ቀን አንዲት ላም ከበረት ሰብራ ወጥታ ስላገኘኋት በልቻታለሁ። ይህ ኃጢአት ከሆነ ፍረዱብኝ።” አለ። እነሱም አንበሳን ሲመለከቱት ግርማው እጅግ የሚያስፈራ ስለነበር “በረት ውስጥ መተኛት ሲገባት በረት ሰብራ መውጣቷ የራሷ ጥፋት እንጂ የርስዎ አይደለም።” አሉት። ነብር ደግሞ በፋንታው ተነስቶ “አንድ ቀን ምግብ ፍለጋ ጫካ ስዘዋወር አንድ የፍየል ጠቦት ከእረኞች አምልጦ ጫካ ውስጥ ቅጠል ሲቀነጥስ አግኝቼ እሱን በልቻለሁ። ኃጢአት ከሆነ ፍረዱብኝ።” አለ። እነአንበሳም “ጥፋተኛው ከእረኞች አምልጦ ጫካ የገባው ፍየል እንጂ አንተ አይደለህም።” አሉት።

ጅብ ደግሞ ኃጢአቱን እንዲህ ሲል ተናዘዘ። “አንድ ቀን ሌሊት ምግቤን ፍለጋ መንደር ለመንደር ስዘዋወር አንዲት በግ እቤት ውስጥ ከማደሪያዋ ሆና ነገር ግን ላቷን በቀዳዳ ወደውጭ አስወጥታ አግኝቼ ቆርጬ በልቻለሁ። ኃጢአት ከሆነ ፍረዱብኝ።” አለ። የተቀሩት እንስሳትም “ጥፋቱ ላቷን ከውጭ ያሳደረችው በግ እንጂ ያንተ ስላልሆነ ልንፈርድብህ አንችልም።” አሉት።

በመጨረሻም አህያ ኃጢአቷን ለመናገር ተነሳችን፤ “አንድ ቀን ጌታዬ አንድ ጆንያ ሙሉ እህል አሸክሞኝ ወደገበያ ስሄድ በመንገድ ላይ ዘመድ አጋጠመውና ቆሞ ሲያወራ ወደመንገዱ ዳር ሄጄ ሳር ነጭቼ በልቻለሁ። ይህ ኃጢአት ከሆነ ፍረዱብኝ።” አለች። እነአንበሳም አህያን “በእኛና በወገኖቻችን ላይ ይህን ሁሉ መአት ያመጣሽ አንቺ ነሽ። ምክንያቱም ጌታሽ ከዘመዱ ጋር ሲያወራ ቆመሽ መጠበቅ ሲገባሽ ሳር መንጨትሽ ከፍተኛ ኃጢአት ነው።” ብለው ተከፋፍለው በሏት ይባላል።

(ምንጭ፡- ፈቃደ አዘዘ፣ የስነ-ቃል መምሪያ፣ 1991ዓ.ም፣ ገጽ78 ለንባብ ትምህርት ማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

## የምዕራፍ ስምንት የክለሳ ጥያቄዎች

1. የሚከተሉትን ስሞች፣ ገላጮች እና ግሶችን በማጣመር ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ረጅም | ከተማ | ቀይ | ጀግና |
| እናት | ነው | አለችኝ | ቀሚስ |
| ውብ | አየሁ | ፎቅ | ለብሳለች |

2. ከአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ጋር በመሆን ስለትምህርት ቤታችሁ የተማሪዎች ሕግና ደንብ በተመለከተ በክፍላችሁ ውስጥ ንግግር በማድረግ በተወያያችሁት መሰረት በክፍል ውስጥ መከበር ያለባቸውን ሕጎች በሚገባ በመጻፍ በክፍል ውስጥ ለሁሉም ተማሪ በሚታይ ቦታ እንዲለጠፍ አድርጉ፡፡
3. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ስለትምህርት ቤታችሁ የተማሪዎች ህግ እና ደንብ በሰንደቅ ዓላማ መርሀ-ግብር ላይ ንግግር አቅርቡ፡፡
4. የሚከተሉት ቅጥያዎች የመነሻ ወይም የመድረሻ ቅጥያዎች መሆናቸውን በመለየት ከቃላት ጋር በማጣመር ጻፉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| - ኣቸው | እንደ- | -ኣዊ | - ኦች |
| በ- | - ዎች | ስለ - | ከ- |

አማርኛ
፬ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ዘጠኝ
## መገናኛ ብዙኃን

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- በመቅረጸ ድምጽ ያዳመጣችሁትን ዋና ሃሳብ ትናገራላችሁ፤
- አንብባችሁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ትሰራላችሁ፤
- ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንቀጽ ትጽፋላችሁ፤
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- ጥገኛ መስተጻምርን ተጠቅማችሁ ዓረፍተ ነገር ታዋቅራላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### የሚኒ ሚዲያዋ ፍሬ



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. በትምህርትቤታችሁ ምን ምን ክበባት አሉ? ዘርዝሯቸው፡፡
ለ. ከርዕሱ በመነሳት ምንባቡ ምን ሊነግራችሁ ይችላል?

ሀ.ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በቃል አብራሩ፡፡

1. ኤደን በስራዋ ምን አይነት ሰራተኛ ናት?
2. በክበባት መሳተፍ የጀመረችው የስንተኛ ክፍል ተማሪ እያለች ነበር?
3. ኤደን ዜና ለማቅረብ ወደ መድረክ ስትወጣ ተማሪዎች የሚያጨበጭቡላት ለምን ይመስላችኋል?
4. በትምህርት ቤታችሁ የሚኒ-ሚድያ ክበብ ምን ዓይነት ስራ ይሰራል? እናንተስ ትሳተፋላችሁ?
5. የሚኒ-ሚድያ ክበብ ተሳትፎዋ አሁን ለደረሰችበት ስኬት ምን አስተዋጽኦ አድርጎላታል ትላላችሁ?

---

## ቃላት

ሀ.በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ሽልማት | ሀ. ከበሬታ |
| 2. ግንባር ቀደም | ለ. ማበረታቻ |
| 3. አንቱታ | ሐ. ታታሪ |
| 4. ስኬታማ | መ. ፊት መሪ |
| 5. ወቅት | ሠ. ጊዜ |
| | ረ. ውጤታማ |

---

ለ. በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ"ለ" ረድፍ ተቃራኒያቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መሸ | ሀ. ሁካታ |
| 2. አበቃ | ለ. ሰጠ |
| 3. ፀጥታ | ሐ. ነጋ |
| 4. ተቀበለ | መ. ከለከለ |
| 5. አበረከተ | ሠ. ጀመረ |

ሐ.የሚከተሉትን አገላለጾች በተሰጡት ቃላት አሚሉ፡፡

| ጸጉር | ጠላ | ጥርስ | ውሃ | አፍንጫ | ቡና | አይን |
|---|---|---|---|---|---|---|

ምሳሌ;- የፈረስ ጭራ የመሰለ_____ቡና_____

1. በረዶ የመሰለ____________________
2. ስንደዶ የመሰለ____________________
3. የዶሮ ዓይን የመሰለ_______________
4. የባቄላ አበባ የመሰለ_______________
5. ጥቁር ሀር የመሰለ_______________
6. ኩል የመሰለ____________________

ሀ.በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ወደረኛ እና ጥገኛ መስተፃምሮች ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ሬድዮ እና ቴሌቪዥን የመገናኛ ብዙሃን አይነቶች ናቸው፡፡ = እና

ለ. በባቡር መሄድ ደስ ይለኛል፡፡ = በ

1. ፋጡማ ከትምህርትቤት መጣች፡፡
2. ትምህርቴን ስጨርስ በመምህርነት ሙያ እሰማራለሁ፡፡
3. ወተት በዳቦ እወዳለሁ፡፡
4. ጎበዝ እና ጨዋ ተማሪ መሆን ይኖርብናል፡፡
5. በስፖርት ውድድር ትምህርትቤታችን አሸናፊ ሆነ፡፡
6. ለጓደኛዬ ጥሩ መሆን አለብኝ፡፡
7. እርሳስ ወይም እስኪርብቶ አውሰኝ፡፡

---

ጽሕፈት

ሀ.የሚከተሉትን ወደረኛ መስተፃምሮች በመጠቀም በእያንዳንዳቸው ሶስት፤ ሶስት ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡

እና ወይም

---

መ.በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ለይታችሁ አውጡ፡፡

ምሳሌ፡- አባቴ ነጋዴ ነው፤ ይሁን እንጂ ስኬታማ አይደለም፡፡ = ይሁን እንጂ

1. ዛሬ ደብተራችን ይታረማል፤ ምክንያቱም ትናንት የቤትስራ ተሰጥቶናልና፡፡
2. ጋዜጠኛው በጣም ጎበዝ ነው፤ በመሆኑም ሽልማት ይገባዋል፡፡
3. ቃሪያ መመገብ እወዳለሁ፤ ነገር ግን ያቃጥለኛል፡፡
4. ማንበብ ያስደስተኛል፤ ይሁን እንጂ ዝምብዬ ጊዜዬን ማባከን አልወድም፡፡
5. መምህራችን ጨዋ ተማሪዎችን ያበረታታሉ፤ ስለዚህ ሁላችንም ጨዋዎች መሆን አለብን፡፡

---

## ንባብ

# የሚዲያ ኮከቦች

## ቅድመ ንባብ

ሀ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን የሚነግራችሁ ይመስላችኋል?
ለ. መገናኛ ብዙኀን ማለት ምን ማለት ነው የምታቁትን ተናገሩ።

### መዓዛ ብሩ



ጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ የወጣቶች ተምሳሌት፣ የሴቶች አርአያ፣ የብርታት ማሳያ፣ የሬዲዮ ፈርጥ፣ የጋዜጠኝነት ምልክት ናት በማለት አድናቂዎቿ እና የሙያ አጋሮቿ ይመሰክራሉ። መዓዛ የዛሬ 20 ዓመት ገደማ የመጀመሪያው ኤፍ.ኤም.ሬዲዮ ጣቢያ ኤፍ.ኤም.አዲስ 97.1 ሲመሰረት የቅዳሜ ከሰዓት በኋላ የጨዋታ ፕሮግራም በዚሁ ጣቢያ ማቅረቧን ተያያዘችው። ይህንን አቅም በመጠቀም በኢትዮጵያ ሚሊኒየም ማገባደጃ ሰሞን በሀገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የግል ይዞታ የሆነውን ሸገር ኤፍ.ኤም 102.1 ሬድዮ ጣቢያን መሰረተች። ሬዲዮው በኢትዮጵያ ተወዳጅ ሆኖ እንዲቀጥል ከፍተኛ ጥረት አደረገች። በዚህ ምክንያት የዓለም ሬዲዮ ቀን በሚከበርበት በ2012 ዓ.ም በሬድዮ ዘርፍ የህይወት ዘመን ምርጥ ጋዜጠኛ ሆና ተሸለመች።

## ደጀኔ ጥላሁን



ጋዜጠኛ ደጀኔ ጥላሁን የተወለደው በ1948 ዓ. ም በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ አዲሱ ገበያ በሚባል አካባቢ ነው፡፡ የጋዜጠኝነቱን ዓለም ከመቀላቀሉ በፊት በመምህርነት ሙያ ያገለገለው ደጀኔ፤ ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ስሙን በጋዜጠኝነት ዓለም የተከለ ባለሙያ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሬድዮ ብሔራዊ አገልግሎት በቆየባቸው 26ዓመታ የጋዜጠኝነት ህይወቱ፤ በተለይም “ከመጽሀፍት ዓለም” በተሰኘ ፕሮግራም ላይ በማራኪ ድምጹ በተረካቸው አያሌ መጽሐፍት ብዙዎች ያስታውሱታል፡፡ ከተለያዩ የጥበብ ባለሙያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ በርካታ የኪነ-ጥበብ ስራዎችንም ሰርቷል፡፡ “የኪነ-ጥበባት ምሽት”ና “የእሁድ ጧት ፕሮግራም” ማዘጋጀት እና ማቅረብ ሌላኛው የሚታወቅበት ስራው ነበር፡፡ አንጋፋው ጋዜጠኛ ደጀኔ ጥላሁን ከመስከረም 2004 ዓ.ም ጀምሮ “ደጀኔ ጥላሁን ፕሮሞሽን” በሚል ድራማ፣ ማስታወቂያ እና ዶክመንተሪ ፊልሞችን በመስራትና በሌሎች መሰል ተግባራት ላይ መሰማራቱ ይታወቃል፡፡

ሀ. ጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ በመጀመሪው ኤፍ.ኤም 97. 1 የጀመረችው ፕሮግራም ምን የሚል ነበር?
ለ. ጋዜጠኛ ደጀኔ ጥላሁን የጋዜጠኝነት ሙያውን የተቀላቀለው በስንት ዓ.ም ነው?



በኢትዮጵያ ሬድዮ ሲቀርቡ በነበሩት "በሕይወት ዙሪያ"፣ "የሴቶች መድረክ"፣ “የእሁድ ጠዋት ፕሮግራም" ላይ ድምጿን ደጋግመን ስንሰማው ኖረናል፡፡ የኢትዮጵያ ሬድዮ ፕሮግራም በሆነው ተወዳጁ "ኢትዮጵያን እንቃኛት" የሬድዮ ፕሮግራም ሲነሳ አብረው ከሚታወሱ ድምጾች አንዱ የእሷ ድምጽ ነው፡፡ በረጅም የጋዜጠኝነት ሥራ ዘመኗ ብዙዎች የሚያስታውሷት በየሳምንቱ እሁድ ረፋድ ላይ ይደመጥ በነበረው የጦር ኃይሎች የሬድዮ ፕሮግራም ላይ ነው፡፡ ፀሐይ እንደጋዜጠኛ ማራኪ ፕሮግራም

ቀማሪ፤ እንደ ሴት ደግሞ ፅናት አስተማሪ ናት። በ2012 ዓ.ም የዓለም ሬዲዮ ቀን ሲከበር ጋዜጠኛ ፀሐይ ተፈረደኝ በሬድዮ ጋዜጠኝነት ላደረገችው ከፍ ያለ አስተዋፅዖ የህይወት ዘመን ምርጥ ጋዜጠኛ ተሸላሚ እንድትሆን ተመርጣለች።

ደምሴ ዳምጤ



የኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኞች ታሪክ ሲጠቀስ ከማይዘነጉት አንዱ ደምሴ ዳምጤ ነው። ደምሴ ከልጅነቱ ጀምሮ ያደረበትን የስፖርት ፍቅር በማጎልበት በ1968ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በኢትዮጵያ ሬድዮ በቋሚነት መስራት ጀመረ። ደምሴን አንስቶ 1980 ዓ.ም የምስራቅና የመካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ ጨዋታ በተለይም የኢትዮጵያና የዝምባቡዌ የፍፃሜ ጨዋታ አለማንሳት አይቻልም። የዋንጫ ጨዋታው የተጠናቀቀው በመለያ ምት ነበር። ይህን ታሪካዊ ጨዋታ ያስተላለፈበት መንገድ ከማንም አዕምሮ አይጠፋም። ሌላው ደምሴ በስራ በቆየባቸው ከ30 አመታት በላይ ከሚታወሱት ስራዎቹ ውስጥ በባርሴሎና ኦሎምፒክ ደራርቱ ቱሉ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ስታሸንፍ ውድድሩን በቢ.ቢ.ሲ ሬዲዮ ሌሊቱን ሙሉ ተከታትሎ በማለዳው ለኢትዮጵያ ህዝብ በአስደናቂ አቀራረብ የምስራቹን አበሰረ፡ ይህን ታላቅ የስፖርት ሰው በህይወት ካጣነው ጥቅምት 26/2014ዓ.ም ዘጠነኛ አመቱን ይዟል።

እሌኒ መኩሪያ



በ1957 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ስራውን በይፋ ሲጀምር በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብላ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ የታየችው ኢትዮጵያዊት ሴት ጋዜጠኛ እሌኒ መኩሪያ ነበረች። ጋዜጠኛ እሌኒ በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ታሪክ ውስጥ ደማቅ አሻራ አላት። በእንግሊዝኛ ቋንቋ የጋዜጠኝነት ሙያ ከኢትዮጵያ እስከ እንግሊዙ ቢ.ቢ.ሲ ሬድዮ በወርቃማ ድምጿ አገልግላለች። ቢ.ቢ.ሲ ላይ አፍሪካዊቷ ኮከብ የተባለች ጋዜጠኛ ነበረች።

(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሬዲዮ 80ኛ ዓመት የተዘጋጀ ልዩ መጽሔት፤ 2013 ዓ.ም)

ሀ.በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡

1. ጋዜጠኛ ደጀኔ ጥላሁን በማራኪ ድምፁ መጽሀፍትን በመተረክ የሚታወቅበት ፕሮግራም ምን ይባላል?

ሀ. ኢትዮጵያን እንቃኛት ለ. ከመጽሐፍት ዓለም

ሐ. የኪነ-ጥበባት ምሽት መ. ጨዋታ

2. የ1980 ዓ.ም የኢትዮጵያና የዝምባቡዌ የምስራቅና የመካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ ጨዋታ የዘገበው ጋዜጠኛ ________________ይባላል፡፡

ሀ. መዓዛ ብሩ ለ. ፀሐይ ተፈረደኝ ሐ. ደጀኔ ጥላሁን መ. ደምሴ ዳምጤ

3. "ኢትዮጵያን እንቃኛት" የሬድዮ ፕሮግራም ሲነሳ አብረው ከሚታወሱት ድምጾች አንዱ የጋዜጠኛ ________________ድምጽ ነው፡፡

ሀ. መዓዛ ብሩ ለ. ፀሐይ ተፈረደኝ ሐ. እሌኒ መኩሪያ መ. ደጀኔ ጥላሁን

4. ________ለመጀመሪያ ጊዜ በቴሌቪዥን መስኮት ለህዝብ የታየች ኢትዮጵያዊት ሴት ጋዜጠኛ ነት፡፡

ሀ. መዓዛ ብሩ ለ. ፀሐይ ተፈረደኝ ሐ. እሌኒ መኩሪያ መ. "ሀ" እነ "ለ" መልስ ነው

5. ጋዜጠኛ ____________የመጀመሪያ የግል ይዞታ የሆነውን ሸገር ኤፍ ኤም 102.1 ሬድዮ ጣቢያን መሰረተች፤

ሀ. መዓዛ ብሩ ለ. እሌኒ መኩሪያ ሐ. ማህደር ሰሎሞን መ. ፀሐይ ተፈረደኝ

## መናገር

መምህራችሁ በሚያስደምጧችሁ መረጃ መሰረት የመረጃውን ዋና ሃሳብ በመለየት ንግግር አድርጉ፡፡

## ቃላት

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

1. ፅናት
2. አስተዋጽኦ
3. አጋር
4. ማገባደጃ
5. መዘንጋት
6. ማኅልበት

ለ.ቀጥሎ በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ደማቅ | ሀ. ነቀለ |
| 2. መጨረሻ | ለ. አስቀያሚ |
| 3. ተከለ | ሐ. ደብዛዛ |
| 4. ማራኪ | መ. መዘንጋት |
| 5. ማስታወስ | ሠ. መጀመሪያ |

## ጽሕፈት

ሀ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮች መስርቱ።

1. መርሃ-ግብር
2. አበሰረ
3. አሻራ
4. ኮከብ
5. ማስተዋል
6. መምህር

ለ.በምሳሌው መሰረት ከታች ባለው ሳጥን ውስጥ የተዘረዘሩትን ግሶች በመጠቀም ነጠላ ዓረፍተነገሮች መስርቱ።

ምሳሌ:- መምህሩ ተማሪዎችን አስተማረ።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አስተማረ | ጻፈ | አመነ | መጠጠ | መሰከረ | ነገደ | ቀጠፈ | ሞረደ |

ሐ.ቀጥሎ በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም ሦስት የተለያዩ ውስብስብ ዓረፍተነገሮች በምሳሌው መሰረት መስርቱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በዓላትን | ይዞ | ለወላጆቻችን | ወንድሙን | ጨዋታ |
| አስጨርሶ | ተሰባስቦ | ሰኞ ማክሰኞ | ማክበር | ምርቃት |
| አጠናን። | ተቀበልን። | እመለሰ። | ተጫውተን | በመታዘዝ |
| | | ደስ ይላል። | | |

ምሳሌ፡- በዓላትን ተሰባስቦ ማክበር ደስ ይላል።

---

መ. በምሳሌው መሰረት ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጻፉ።

ምሳሌ፡- የልጆች ጨዋታ -?"መጩ ተኬ"

መጩ ተኬ አንዱ የልጆች ጨዋታ ነው። ለጨዋታው ቢያንስ ሁለት ልጆች ያስፈልጋሉ፡ ለመጫወቻ የሚሆን ከእጃችን መዳፍ የሚያንስ ሁለት ጠፍጣፋ ድንጋይ እናዘጋጃለን። የድንጋዩ ስም “ከምች” ይባላል። ጨዋታውን አንዱ ልጅ ቀድሞ ይጀምራል። ጨዋታውን የሚጀምረው ልጅ አንዱን ድንጋይ (ከምች) መሬት ላይ በተወሰነ ርቀት ይጥለዋል። ድንጋዩን በሌላ ድንጋይ (ከምች) ይመታዋል ወይም ያጋጨዋል። ድንጋዩን ከመታው ጓደኛው ያዝለዋል። የተመታው ድንጋይ ድረስም ይወስደዋል። ከሳተው ደግሞ ጓደኛውን ያዝለዋል። የሳተው ድንጋይ ድረስ ይወስደዋል። በዚህ ህግ ተራ በተራ ጨዋታው ይቀጥላል።


---

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ፡፡**

### ስግብግቡ አይጥ







አንድ ስግብግብ አይጥ በበቆሎ የተሞላ ቅርጫት አየና ሊበላ ፈለገ፡፡ ስለዚህ ቅርጫቱን በጥርሱ ቦርቡሮ ትንሽ ቀዳዳ ሠራ፡፡ በዚያች ቀዳዳም ወደቅርጫቱ ውስጥ ገባ፡፡ በዚያ ውስጥም ሆኖ ብዙ በቆሎ በላ ከዚያ በጣም ተደሰተ፡፡ እንደልቡ መጥገቡን ሲያረጋግጥ ለመውጣት ፈለገ፡፡ አስቀድሞ በሰራት በትንሿ ቀዳዳ በኩል ለመውጣት ሞከረ፡፡ ግን አልቻለም፡፡ ሆዱ ሞልቷል፡፡ እንደገና ሞከረ፡፡ ግን በቀዳዳው አልፎ መውጣት አልቻለም፡፡ አይጡ ማልቀስ ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ጥንቸል በቅርጫቱ አጠገብ እያለፈ ነበር፡፡ የአይጡን ጩኸት ሰምቶ “ወዳጄ ለምን ታለቅሳለህ?” አለው፡፡ ያኔ አይጡ “በቆሎውን ለመብላት ብዬ ትንሽ ቀዳዳ ሰርቼ ወደ ቅርጫቱ ውስጥ ገባሁ፤ አሁን በዚያ ቀዳዳ በኩል መውጣት አልቻልኩም፡፡” አለ፡፡ ጥንቸሉም “ብዙ ስለበላህ ነው፤ ሆድህ እስኪቀንስ ጠብቅ፡፡” ብሎት እየሳቀ ሄደ፡፡ አማራጭ ያጣው አይጥ በቅርጫት ውስጥ እንዳለ እንቅልፍ ያዘው፡፡ በማግስቱ ጠዋት ሆዱ ቀንሷል፡፡ እሱ ግን ከቅርጫቱ ውስጥ መውጣት እንዳለበት ረስቶ ጥቂት ተጨማሪ በቆሎ መብላት ፈለገ፡፡ ስለዚህ በቆሎውን በልቶ ሆዱ በድጋሚ ተቆዘረ፡፡ ጠግቦ ከበላ እና ቁንጣን ከያዘው በኋላ ከቅርጫቱ ወጥቶ ማምለጥ እንዳለበት አስታወሰ፡፡ ግን የማይሆን ነገር ነው፤ አልቻለም፤ እናም በድጋሚ “አ! አሁንም ነገ እወጣለሁ፡፡” ብሎ አሰበና ተኛ፡፡ ግን በቀጣዩ ቀን በዚያ የበቆሎ ቅርጫት በኩል ታልፍ የነበረው ድመት ነበረች፡፡ ምን ያጋጥመው ይሆን?



(ምንጭ፡- NeBeb ንበብ፡ Reading Platform ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተሻሽሎ የቀረበ)

## መናገር

የሚከተሉትን የሰውነት ክፍሎች በግእዝ ስያሜያቸው ምን እንደሚባሉ ካጠናችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ በቃል አቅርቡ፡፡

| የሰውነት ክፍሎች ስዕል | | ግእዝ | የሰውነት ክፍሎች ስዕል | አማርኛ | ግእዝ |
|---|---|---|---|---|---|
|  | ራስ | ርእስ |  | አፍ | አፍ |
|  | ፀጉር | ስእርት |  | ከንፈር | ከንፈር |
|  | ፊት | ገጽ/መልታሕት |  | ጥርስ | ስን |
|  | ግንባር | ፍጽም |  | አገጭ | ሕልቅ |
|  | ዐይን | ዐይን |  | ጣት | አፃብዕ |
|  | | ቀርነብ |  | ጉልበት | ብረክ |
|  | ጆሮ | እዝን |  | እጅ | እድ |
|  | | አንፍ |  | እግር | እግር |

(ምንጭ፡- መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃለት ሐዲስ፤ 1948ዓ.ም)

## የምዕራፍ ዘጠኝ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሃጫ | ደንብ | ገለጸ |
| ለሆሳስ | ስውር | ወጠነ |

2. ጥገኛ መስተጻምሮችን በመጠቀም አምስት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

3. የሚከተሉትን አገላለጾች አሟሉ፡፡

ምሳሌ፡- ሎሚ የመሰለ ተረከዝ ካልን፡-

ሀ. ድሪ የመሰለ______________እንላለን፡፡

ለ. ሳንቃ የመሰለ______________እንላለን፡፡

ሐ. ብርሌ የመሰለ_____________እንላለን፡፡

መ. አለንጋ የመሰለ_____________እንላለን፡፡

4. ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥን ወይም ከሌሎች የመገናኛ ብዙሃን የሰማችሁትን አስተማሪ መረጃ ከ5 እስከ 7 በሚሆኑ ነጠላ ዓረፍተነገሮች በመጠቀም በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

አማርኛ
፬ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አስር
## ንግድ

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- አዳምጣችሁ በቡድን ውይይት ታደርጋላችሁ፤
- ካነበባችሁት ጽሁፍ ውስጥ ከእያንዳንዱ አንቀጽ ዋናውን ሃሳብ ትለያላችሁ፤
- በተሰጣችሁ ርዕስ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፤
- ከአንድ በላይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት ትፈልጋላችሁ፤
- ቅጥያዎችን ተጠቅማችሁ አረፍተነገር ትመሰርታላችሁ፤

## ማዳመጥ

### ንግድ



**ቅድመ ማዳመጥ**

ሀ. ንግድ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. በምትኖሩበት አካባቢ የንግድ ተቋማት አሉ? ካሉ ምን ምን አይነት የንግድ ተቋማት እንደሆኑ ተናገሩ?

**ሀ.ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በቃል አብራሩ፡፡**

1. አንድ ነጋዴ ትርፋማ ለመሆን ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?
2. ነጋዴ ኪሳራ የማይገጥመው ምን ሲሆን ነው?
3. ደንበኛን በጥሩ ስነ-ምግባር ማስተናገድ ለምን የሚጠቅም ይመስላችኋል?
4. ገንዘብ ብቻ መኖሩ ለስኬት አያበቃም ሲል ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ፡፡
5. የንግድ ስራ ለአንድ አገር የሚሰጠውን ጥቅም ተናገሩ፡፡

---

**ቃላት**

**ሀ.በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መመዘኛ | ሀ. ችሎታ |
| 2. ውል | ለ. ማፍለቅ |
| 3. መፈለግ | ሐ. መለኪያ |
| 4. ማመንጨት | መ. መሻት |
| 5. ክህሎት | ሠ. ስምምነት |

ለ.በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ"ለ" ረድፍ ተቃራኒያቸውን በመምረጥ አዛምዱ

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አተረፈ | ሀ. ተጎዷ |
| 2. ተጠቃሚ | ለ. ማሕበራዊ |
| 3. ውጫዊ | ሐ. መጓደል |
| 4. ግላዊ | መ. ከሰረ |
| 5. መሟላት | ሠ. መውጣት |
| | ረ. ውስጣዊ |

## ጽሕፈት

ሀ.ከዚህ በታች በቀረበው የአንቀጽ ምሳሌ መሰረት የተከታዩን አንቀጽ ዋና መልዕክት(ሃሳብ) ጻፉ።

ምሳሌ፡-

እኛ ኢትዮጵያውያን በአብሮነት አኗኗራችን ከመሰረትናቸው ጠንካራ እሴቶቻችን መካከል አንዱ በሀዘን ጊዜ መደጋገፍ እና እርስ በእርስ መጽናናት ነው። ለዚህም ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ደግሞ ማህበራዊ መሰባሰቢያችን የሆነው እድር ነው። እድር መግባት ሃላፊነት እና ግዴታ የሚያስከትል ቢሆንም ሰው ሆኖ የማይደሰት እንደሌለ ሁሉ ሃዘን የማይገጥመው የለም። ታዲያ በዚህ ጊዜ ያዘነ ሰው ከሃዘኑ እንዲላቀቅ ለማጽናናት ብሎም ከሃዘን ጋር ተያይዞ ለሚገጥመው ወጪ ድጋፍ እና አለው ባይነትን ከማህበረሰቡ የሚያገኝበት እርስ በእርስ የምንተጋገዝበት ትልቅ ኢትዮጵያዊ የማህበራዊ አብሮነት ማሳያ መሰባሰቢያችን የሆነው እድር ነው።

የአንቀጹ ዋና መልዕክት፡- የኢትዮጵያዊ አብሮነት ማሳያዎች ከሆኑት አንዱ እድር መሆኑን እና ያለውን ጠቀሜታ የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህ በታች የተጻፉት አንቀጾች ዋና ሃሳባቸው ምንድን ነው?


1. ገበጣ የኢትዮጵያ ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡ ይህን ጨዋታ ሁለት ሰዎች የሚጫወቱት ነው፡፡ በገበጣ ጨዋታ ህግ መሰረት ገበቴው ላይ 18 ጉድጓዶች ሲኖሩ የተወሰኑ ጠጠሮችም በየጉድጓዱ ይቀመጣሉ፡፡ የጨዋታው አላማ እንግዲህ የተወዳዳሪውን ጠጠሮች መብላት ነው፡፡ የተወዳዳሪው ጠጠሮች ዜሮ ሲቀሩ ያንጊዜ ተጫዋቹ አሸነፈ ይባላል፡፡




2. ትምህርት ቤት ገብተን የመማሪያ ሰዓት ኖሮት በሙያው ላይ የሰለጠኑ መምህራን ተመድበውለት የሚሰጥ ትምህርት መደበኛ ትምህርት ይባላል፡፡ በአገራችን መደበኛ ትምህርት ከአጸደ ሕጻናት ጀምሮ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ የሚሰጥ ሲሆን ዋና አላማው ሰዎች የሚጠቀሙበትን እውቀት እና ክህሎት ማስጨበጥ ነው፡፡


---

ለ.በምሳሌው መሰረት ከታች የተሰጠውን ምስል በመመልከት በእያንዳንዱ ምስል አንድ፤ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡



ይህ ምስል የሚያሳየን የእንስሳቱን እና የዕጽዋቱን የምግብ ሰንሰለት ትስስር ነው፡፡ በትስስሩ መሰረት ህይወት ካላቸው አራቱ ነገሮች መካከል በቅድሚያ እጽዋቱ ለመኖር የተለያዩ መዓድናትን እና ውሃን በስሩ አማካኝነት ከመሬት በማግኘት እና በፀሀይ ብርሃን ምግቡን በማዘጋጀት ያድጋል፡፡ አይጥ ደግሞ በህይወት ለመቆየት እጽዋቱን ይበላል፡፡ ምክንያቱም አይጥ ስጋ እና እጽዋትም ተመጋቢ በመሆኑ፡፡ በመቀጠል እባብ አይጡን ይውጣል፡፡ በተመሳሳይ እባቡ ደግሞ በጭልፊት (አሞራ) ይበላል ማለት ነው፡፡

1. 

2. 

## ንባብ

### ከታታሪነት እስከ ለጋሽነት



## ቅድመ ንባብ

ሀ. አንድ ሰው መልካም ሰው የሚባለው ምን አይነት ተግባራትን ሲፈጽም ነው?

ለ. እናንተ የፈጸማችሁት መልካም ተግባር ካለ ተናገሩ?

ሱራፌል ይባላል፡፡ ሱራፌል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ካሉ የትላልቅ ሆቴሎች ባለሀብቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ሱራፌል ከሆቴል ንግድ ስራው ጎን ለጎን በበጎ አድራጎት እና በከተማ ልማታዊ ስራዎች ላይም ይሳተፋል፡፡ ዛሬ ከደረሰበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት ከልጅነቱ ጀምሮ በየመንገዱና በየመኪናው መስኮት እየዞረ ማስቲካ፣ ሶፍት እና ብስኩት በመሸጥ የሚያገኘውን ትርፍ በማጠራቀም ዘወትር ቅዳሜ ቅዳሜ ባንክ እየሄደ ያስቀምጥ ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ለተከታታይ አምስት አመታት ያስቀመጠው ገንዘብ ስልሳ ሺህ ብር ደረሰለት፡፡ ከዚህ በኋላ “በዚህ ገንዘብ ተጨማሪ ስራ ብሰራበት ይሻላል፡፡” በሚል ባንክ ካጠራቀመው ስልሳ ሺህ ብር ላይ ሃምሳ ሺህ ብር በማውጣት በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅቶ በተሰጠው ትንሽ ብረት በብረት የሆነች ቤት ውስጥ ቁርስ ቤት ከፈተ፡፡ በከፈተው ቁርስ ቤት እንደ ቡና፣ ሻይ፣ ወተት የመሳሰሉትን ትኩስ ነገሮችንና እንዲሁም ሽሮ፣ ፍርፍር፣ ብስኩት እና ዳቦ የምግብ ዓይነቶችን እያዘጋጀ መስራት እና መሸጥ ጀመረ፡፡ የሚያዘጋጀው ምግብ ጥራት ስለነበረው ከሩቅም ከቅርብም ደንበኛ በርከትከት ማለት ጀመረ፡፡ በሃምሳ ሺህ ብር የጀመረው ቁርስ ቤት ገቢውን ከማሳደግ አልፎ ከብዙ ሰዎች ጋር እንዲተዋወቅ አደረገችው፡፡

ሀ ባለታሪኩ ካለው የስራ ፍላጎት በመነሳት ንግዱ የት ደረጃ የሚደርስ ይመስላችኋል?

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ተጨማሪ ገንዘብ ከባንክ ብድር ወስዶ ከቁርስ ቤቷ በተጨማሪ ሰፋ ያለ ቤት ተከራይቶ የሆቴል ንግድ ስራን ተያያዘው፡፡ ለወትሮውም ስሙ-ጥርና ታታሪ የነበረው ሱራፌል ዝናውን የሰሙ ሰዎች ወደሆቴሉ መጉረፍ ጀመሩ፡፡ በሆቴል ስራውም ከራሱ አልፎ በውስጡ ከሃያ በላይ ለሚሆኑ ወጣቶች የስራ እድል መፍጠር ቻለ፡፡ ከመንግስት የሚጠየቀውን ግብርም በሰዓቱ ስለሚከፍል በየአመቱ በርካታ የምስክር ወረቀት ይሸለማል፡፡

ትናንት በየመንገዱ ማስቲካና ሶፍት እያዞረ ሲሸጥ የነበረው ሱራፌል የሚያገኘውን ገቢ በአግባቡ በመቆጠቡ ዛሬ የትልቅ ሆቴል ባለቤት ለመሆን በቅቷል፡፡

ሱራፌል ከንግድ ስራዉ ጎን ለጎን በክፍለ ከተማው የሚገኙ ባለሀብቶችንና የመንግስት ባለስልጣናትን በማወያየት የህፃናት መርጃ ድርጅት የሚል የበጎ አድራጎት ማሕበር አቋቁሟል፡፡ ከ150 በላይ የሚሆኑ ሕፃናትንም በሕፃናት መርጃ ድርጅቱ ውስጥ በማቀፍ ከዕለት ጉርሳቸው እስከ አመት ልብሳቸው አልፎ ተርፎም የትምህርት ቁሳቁሳቸውን ሁሉ ያሟላላቸዋል፡፡

የተለያዩ የልማት ስራዎች በሚሰሩበት ጊዜም የአካባቢውን ማህበረሰብ በማስተባበር በኩል የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል፡፡ በመሆኑም በዚህ አመት ለደረሰበት መልካም ውጤት ሽልማትን ተቀበለ፡፡

**ሀ.ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. ሽልማት የተሰጠው ምን አይነት ስራ ስለሰራ ነው?
2. ባለታሪኩ በልጅነቱ ምን አይነት ስራ ይሰራ ነበር?
3. ገንዘብ መቆጠብ ለምን ይጠቅማል?
4. ሱራፌል ሕዝቡን በማስተባበር በኩል <<ያንበሳውን ድርሻ ይወስዳል>> ሲል ምን ለማለት ነው?

---

## መናገር

የምንባቡን ዋና መልዕክት ወይም ሃሳብ በአምስት ዓረፍተ ነገሮች አጠቃላችሁ ጻፉ፡፡ በመቀጠል ስለዋናው መልዕክት የቡድን ውይይት በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ አቅርቡ፡፡

---

## ቃላት

**ሀ.በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መጉረፍ | ሀ. መልካም |
| 2. ማቀፍ | ለ. ማጠራቀም |
| 3. በጎ | ሐ. በብዛት መምጣት |
| 4. በረከተ | መ. መያዝ |
| 5. መቆጠብ | ሠ. በዛ |

---

ለ.ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

1. ልማት
2. አወጣ
3. አመት
4. አተረፈ
5. መቅረት

---

ጽሕፈት

ሀ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚያሳዩትን ትርጉም በዓረፍተ ነገር ውስጥ በመጠቀም አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡-

- ✓ ከመጫወት ይልቅ ስራችንን በአግባቡ እንስራ፡፡ (ሲጠብው = እናከናውን/ እንተግብር)
- ✓ እንስራ ከሸክላ አፈር የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ (ሲላላ = ለውሃ መያዣነት የሚያገለግል ባህላዊ ቁስ)

1. ገዳም
2. ጥሬ
3. ግጥም
4. ወጥ

---

ለ. ከሚከተሉት ባለቅጥያ ቃላት ውስጥ ቅጥያዎችን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ውጤታማ | ልብሳቸው | ግበዓት | መኪናዬ | ዶሮዎች | ሴትነት |
| | | ቤታችን | ፈረሶች | | |

ምሳሌ፡- ውጤታማ = ውጤት - ኣማ

---

ሐ. በሳጥኑ ውስጥ የተዘረዘሩትን ስም፣ ግስ፣ ቅፅል(ገላጭ)፣ እና መስተፃምር መሆናቸውን ለይታችሁ በየምድባቸው አስቀምጡ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አተረፈ | ነጋዴ | ረጅም | ተራራ | ወይም |
| ገበያ | ጠይም | እና | አስተማረ | ገመጠ |

**ቅጽል**

1.
2.
3.

**ስም**

1.
2.
3.

**ግስ**

1.
2.
3.

**መስተጻምር**

1.
2.
3.

---

መ. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሹካዎች | መንደራችን | መምህሮች | ነጻነት | ትርፋማ |

| | |
|---|---|
| መንገደኛ | መንፈሳዊ |

ምሳሌ፡- በመደርደሪያው ላይ በርካታ ሹካዎች ተቀምጠዋል።

---

ሠ.በምሳሌው መሰረት የሚከተሉት ቃላት በዓረፍተነገር ውስጥ ሲገቡ የሚሰጡትን የተለያየ ትርጉም የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ደረሰ

- ✓ ወደቤቱ በጊዜ ደረሰ፡፡ (ትርጉሙ =በሰዓቱ ተመለሰ)
- ✓ መጽሐፍ ደረሰ፡፡ (ትርጉሙ= ጻፈ)

1. ጠላ
2. አሰሰ
3. ሳሳ
4. ስጋ
5. ቀጠፈ

---

ረ.ከታች የቀረበውን አንቀፅ በማንበብ አራት ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን አውጡ፡፡

### መርካቶ

መርካቶ በአፍሪካ ትልቁ የገበያ ቦታ ነው፡፡ በዚህ የገበያ ቦታ ውስጥ የማይሸጥ ነገር የለም፡፡ ነጋዴው ሁሉንም የሸቀጥ አይነት ይሸጣል፤ ወዛደሩ ወገቡ እስኪጎብጥ ይሸከማል፡፡ አንዳንዶች ካርቶን ተሸክመው ሲሮጡ፡፡ የተሸከሙት ካርቶን የራስደጀን ተራራ ይመስላል፡፡ ህዝቡ እንደጉንዳን ይርመሰመሳል፡፡ መኪናው ከመብዛቱ የተነሳ መተላለፊያ መንገዶች ተዘግተዋል፡፡ ሻጭና ገዥው ሲገበያይ ስውር ስራቸውን የሚሰሩ የመርካቶ ኪስ አውላቂዎችም አይጠፉምና መጠንቀቁ አይከፋም፡፡

ምሳሌ፡- መርካቶ በአፍሪካ ትልቁ የገበያ ቦታ ነው፡፡

---

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ ምንባብ አንብቡ።

### አህያና ውሻ

በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ አንድ ውሻና አንድ አህያ ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን አህያዋ ለውሻው እንዲህ አለችው። ‹‹እኔ ስራ ስለበዛብኝና እዚህ ቤት መኖር ስለሰለቸኝ ልጠፋ ነው።›› ብላ አማከረችው። ውሻውም ካዳመጣት በኋላ ‹‹እኔም እዚህ ቤት መኖር ሰልችቶኛልና አብሬሽ መጥፋት እፈልጋለሁ።›› አላት። በዚህም ተስማምተው ሁለቱም ጉዟቸውን ጀመሩ። ብዙ ርቀት ከተጓዙ በኋላ ፀሀይ እየጠለቀች ምሽቱ እየገፋ ሲመጣ አንድ ሳር ያለበት ሜዳ ላይ ደረሱ። አህያዋም እርቧት ስለነበረ ሳር መጋጥ ጀመረች። ውሻውግን የሚበላ ነገር ስላላገኘ ሜዳው ላይ ተቀመጠ።

አህያዋ ብዙ ሳር ግጣ ከጠገበች በኋላ ለውሻው ‹‹አንዴ ላናፋ ነው።›› አለችው። ውሻውም ‹‹ምን ነካሽ ! ካናፋሽ በጅብ መበላትሽ ነውና ይቅርብሽ።›› ቢላትም ሜዳውን እየዞረች ካናፋች በኋላ በድጋሚ ሳር መጋጥ ቀጠለች። ለሁለተኛ ጊዜም ስትጠግብ ለውሻው ‹‹ላናፋ ነው።›› ብላው ሜዳውን እየዞረች አናፍታ ስትጨርስ ሳር መጋጧን ቀጠለች። አሁንም ጥቂት ጊዜ ከቆየች በኋላ ውሻውን ‹‹እባክህን ፍቀድልኝና ለመጨረሻ ጊዜ ላናፋ?›› አለችው። ውሻው ግን ‹‹ተይ የመጀመሪያው ማናፋት ለጅቡ መጥሪያ፤ ሁለተኛው ደግሞ ጅቡን ማቅረቢያ፤ በሶስተኛው ግን መበላትሽ ነውና ይቅርብሽ።›› አላት። አህያዋ ግን ምንም አይመጣም ብላ ሜዳውን እየዞረች ድምጿን ከፍ አድርጋ



## የምዕራፍ አስር የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡ በመቀጠልም ዓረፍተነገር መስርቱባቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ባላንጣ | አጣላ | አንጋጠጠ |
| አቀረበ | ሰባ | መራራ |

2. የሚከተሉትን ቃላት በዓረፍተነገሮች ውስጥ ሲገቡ የሚኖራቸውን የተለያየ ትርጉም የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡-

ሀ. ቆረጠ

ለ. ሰፋ

ሐ. ገዛ

መ. ምሳ

ሠ. አረረ

3. የንባብ ጥቅምን የተመለከተ ከ5-7 ዓረፍተነገሮችን የያዘ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

## ቃላት ከነፍቻቸው

| | |
|---|---|
| ህቡዕ | ድብቅ፣ ምስጢር፣ ይፋ ያልሆነ |
| ለቀቀ | በስድ አሳደገ፣ አባለገ፣ ፈታ፣ ነፃ አደረገ፣ ተወ |
| ለተመ | በኃይል አጋጨ፣ መታ |
| ለገሰ | ቸረ፣ ናኘ፣ ሰጠ |
| ሊቅ | በትምህርት የበሰለ፣ የተራቀቀ ምሁር፣ አዋቂ |
| ላቀ | በለጠ፣ አደገ፣ በረታ፣ ከፍ አለ |
| መለሎ | ቀጥ ያለ፣ ረዥም፣ ሽንቅጥ ያለ፣ |
| መረን | ስድ፣ ልቅ፣ አግድም አደግ፣ ባለጌ፣ ያልተቀጣ |
| መሰሪ | ሸረኛ፣ ተንኮለኛ፣ ለበጎም ለክፉም ነገር የሚጠበብ |
| መርሃ-ግብር | የስራ መመሪያ፣ ዕቅድ፣ ፕሮግራም |
| መሻት | መፈለግ፣ መፍቀድ፣ መመኘት |
| መነመነ | ከሳ፣ ቀጠነ፣ ሞገገ፣ ኮሰመነ፣ ሟሸሸ |
| መነዘረ | ሸረፈ፣ ተነተነ፣ ለወጠ፣ በተነ |
| መዘንጋት | መርሳት |
| ረግረግ | ውሃማ ቦታ |
| ራራ | አዘነ፣ ማረ፣ ይቅር አለ |
| ራሰ | ረጠበ፣ ተነከረ |
| ሰለቸ | ታከተ፣ ተንገፈገፈ፣ ተማረረ፣ ተንገሸገሸ |
| ሰመረ | አማረ፣ ተዋጣ፣ ተሳካ፣ |
| ሰረገ | ደገሰ፣ ዳረ፣ ሰመጠ፣ ወደውስጥ ገባ፣ ወደመሬት ውስጥ ገባ |
| ሲሳይ | እህል፣ ምግብ፣ ሃብት፣ አዱኛ፣ በረከት |
| ሳንቃ | ለበር መዝጊያ የሚሆን ጠፍጣፋ እንጨት |
| ሸመተ | ገዛ፣ ገበየ፣ ለወጠ፣ አተረፈ |
| ቀላቀለ | አደባለቀ፣ አገናኘ፣ ቀየጠ |
| ቀማኛ | ወንበዴ፣ ዘራፊ፣ የሚነጥቅ |
| ቅርስ | የሰው፣ የእንስሳት፣ የዕፅዋት ቅሪት፣ የተጠራቀመ ሃብት |

| | |
|---|---|
| በለጸገ | ከበረ፣ ሐብታም ሆነ |
| ተመረቀ | ተባረከ፣ በረከት አገኘ |
| ተጋ | ፈጠነ፣ ነቃ፣ በረታ፣ ኀበዘ፣ ታተረ፣ ከስንፍና ራቀ |
| ታነፀ | ተገነባ፣ ተቀረፀ |
| ትሁት | ቅን፣ ገር፣ ታዛዥ፣ ስነ-ስርዓት አክባሪ |
| ነሰነሰ | ኀዘኀዘ፣ በተነ፣ ረጨ፣ ዘረዘረ |
| ይፋ | ግልፅ |
| ንዋይ | ሀብት፣ ንብረት |
| አለቃ | መሪ፣ ሹም፣ ዋና፣ |
| አላመጠ | አኘከ፣ አደቀቀ፣ በላ፣ ስም አጠፋ፣ አማ |
| አላቀቀ | ለያየ፣ በታተነ፣ ገነጣጠለ |
| አርዓያ | ምሳሌ፣ አብነት፣ አምሳል፣ የመልካም ምሳሌ |
| አበረከተ | ሰጠ፣ አበዛ |
| አያሌ | በጣም ብዙ፣ በርካታ |
| አናፋ | ጮኸ(ለአህያ)፣ ጉራውን ነዛ |
| አንቱታ | ከበሬታ |
| ወላወለ | አመነታ፣ ተጠራጠረ፣ አፀዳዳ፣ ጠራረገ |
| ውብ | ቆንጆ፣ ያማረ፣ ለዛ ያለው |
| ዛለ | ደከመ፣ ተልፈሰፈሰ፣ አቅም አጣ |
| ደባ | ተንኮል፣ ሴራ፣ ክፋት |
| ደንበኛ | ሁነኛ፣ ዘወትር ካንድ መደብር እቃ የሚገዛ |
| ደኀመ | ረዳ፣ ደገፈ፣ በኀደለ ሞላ |
| ድል | ማሸነፍ፣ አሸናፊነት |
| ጀብድ | ጀግንነት፣ ደፋር |
| ጃጀ | አረጀ፣ አፈጀ፣ ሸመገለ |
| ገበያ | መግዣ፣ መሸጫ፣ የንግድ ልውውጥ የሚካሄድበት ቦታ |
| ገባር | መጋቢ |
| ጦስ | ምክንያት፣ መዘዝ፣ ሰበብ፣ |

| | |
|---|---|
| ጫና | ከባድ ሸክም፣ ጭቆና |
| ጮሌ | ብልጥ፣ ፈጣን |
| ፀዳ | ንፁህ ሆነ፣ ነፃ |
| ፀፀት | ሐዘን፣ ንስሐ፣ ትካዜ፣ የቁጭት ስሜት |
| ፅናት | ጥንካሬ፣ ብርታት |
| ፈተነ | ሞከረ፣ ፈተሸ |
| ፈፀመ | ጨረሰ፣ ቋጨ፣ አጠናቀቀ፣ አደረገ፣ ሰራ |
| ፌሽታ | የደስታ መግለጫ፣ፈንጠዝያ |
| ፍርድ | ብይን፣ ዳኝነት፣ ውሳኔ፣ ፍትህ |
| ፍቅር | መውደድ፣ ግብቡ፣ ስምሙ፣ እጅግ በጣም ጥልቅ የሆነ መዋደድ |

# ዋቢ ጽሑፎች


ለማ ጉያ (1995 ዓ.ም)። ያላስተማሪ የሥዕል ትምህርት መማሪያ መጽሀፍ። አ.አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት።

መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃለት ሐዲስ። (1948ዓ.ም)። በአርቲስቲክ ማተሚያቤት ታተመ።

ሺበሺ ለማ(2007ዓ.ም)። አርዓያዎቹ። ሜጋ ኣሳታሚ እና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ ማኅበር።

በትምህርት ቤቶች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማኑዋል።(2011 ዓ.ም)። ንቁ በርታ ማተሚያ ቤት።

በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር። (2009 ዓ.ም)። አጋዥ መጽሀፍ ለንባብ ትምህርት።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር። የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት።(2013ዓ.ም)። ዝክረ ህዳሴ። አዲስ አበባ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርትቢሮ(2004ዓ.ም)። የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ።አል-ጉርኤር አሳታሚ እና አከፋፋይ።

በፎረም ሶሻል ስተዲስ እና በብሪቲሽ ኤምባሲ(በ2007ዓ.ም)። የሕዝብ አገልግሎቶች አሰጣጥ በአዲስ አበባ

ባህሩ ዘርጋው (1994 ዓ.ም)። ዘርጋው መለስተኛ የአማርኛ መዝገበቃላት። ርኆቦት ሚዲያዎች።

ባዬ ይማም (2004 ዓ.ም)። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው። አልፋ ፕሪንተር።

ብርሃኑ ሀብተማሪያም(1997ዓ.ም)። ውሃ ህይወት ነው። በት.መ.ማ.ማ.ድ ታተመ

ተክለማርያም ፋንታዬ(1964ዓ.ም)። ኖኀተ ጥበብ ዘሥነ-ጽሁፍ። ሴንተራል ማተሚያ ቤት።

ቱሪዝም አዲስ 6ኛ ዓመት፣ ቁጥር 8፣ (2001ዓ.ም)፡፡ አዲስ አበባ፡፡

አዲሰ ዘመን ጋዜጣ (2011 ዓ.ም)፡፡ 78ኛ ዓመት፤ መጋቢት 1 ፡፡ ቁጥር 181፡፡

አዲስ ዘመን (2011ዓ.ም)፡፡ 78ኛ አመት ፤ መጋቢት 23ቁጥር 203፡፡

አዲስ ዘመን ጋጤጣ (2012 ዓ.ም)፡፡ 79ኛ ዓመት ሚያዚያ 7፤ ቁጥር 217፡፡

የኢትዮጵያ ሬድዮ ለ80ኛ ዓመት የተዘጋጀ ልዩ መጽሔት (2013ዓ.ም)፡፡

እሸቱ አሰፋ፡፡(2000ዓ.ም)፡፡ <u>ፕላኔቶችና ሌሎች የሰማይት አካላት</u>፡፡

ከህጻናት መዝሙር ላይ የተወሰደ ያልታተመ

ዳንዔል ወርቁ(2011ዓ.ም)፡፡ <u>የጣና አቤቱታ</u>፡፡ ወርልድ ቪዥን፡፡

--------------(2011ዓ.ም)፡፡ <u>ወርቃማው ዓሣ</u>፡፡ ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ፡፡

ፈቃደ አዘዘ (1991ዓ.ም)፡፡ <u>የስነ-ቃል መምሪያ</u>

# የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

## የፊደል ቅደም ተከተል

ሀ. የመጀመሪያ ፊደል = ግዕዝ

ሁ. ሁለተኛ ፊደል = ካዕብ

ሂ. ሶስተኛ ፊደል = ሳልስ

ሃ. አራተኛ ፊደል = ራብዕ

ሄ. አምስተኛ ፊደል = ሀምስ

ህ. ስድስተኛ ፊደል = ሳድስ

ሆ. ሰባተኛ ፊደል = ሳብዕ

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፻ | 100 | ፳፻ | 2000 |
| ፪፻ | 200 | ፴፻ | 3000 |
| ፫፻ | 300 | ፵፻ | 4000 |
| ፬፻ | 400 | ፶፻ | 5000 |
| ፭፻ | 500 | ፷፻ | 6000 |
| ፮፻ | 600 | ፸፻ | 7000 |
| ፯፻ | 700 | ፹፻ | 8000 |
| ፰፻ | 800 | ፺፻ | 9000 |
| ፱፻ | 900 | ፻፻ | 10000 |
| ፲፻ | 1000 | | |

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ